# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 098 ታኅሣሥ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና የኢኮኖሚ ትሩፋቶች

ሞገስ ጸጋዬ

የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ወደ ሥራ ከገባ ጀምሮ ከወጪ ንግድ እና ከተኪ ምርት 2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ገቢ ማስገኘት ችሏል። እንዲሁም በ2016 ሩብ ዓመት ውስጥ ከ23 ሚሊዮን ዶላር በላይ የገቢ ምርትን መተካት የቻለ ሲሆን ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። ነጻ የንግድ ቀጣናው ወደ ሥራ ከገባ ወዲህ ከፍተኛ ሥራ እድልም ፈጥሯል።

ነፃ የንግድ ቀጣናን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማርኬቲንግና ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ሙሉጌታ ግርማ፤ የድሬዳዋ ነጻ ንግድ ቀጣና ለኢኮኖሚ እድገት መሣሪያ ተደርጎ ይወሰዳል ይላሉ። በሥራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ገንዘብ ግኝት፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማምጣት መሠረታዊ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል እንደሆነም ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር ሙሉጌታ ገለጻ፣ እ.ኤ.አ በ2022 ሥራ የጀመረው ነጻ የንግድ ቀጣና በቂ የቅድመ ዝግጅት ሥራ የተደረገበት ነው። በአጭር ጊዜም ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ ነው። የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ከሚዛን ውስጥ በማስገባት የሕግ ማዕቀፍ አውጥቶ ወደ ሥራ የተገባ በመሆኑ ከነጻ ንግድ ቀጣናው ኢትዮጵያ ጥቅም መቋደስ ጀምራለች።

ነጻ የንግድ ቀጣናው ወደ ሥራ ከገባ በኋላ የሥራ እድል ፈጠራ ላይ ያለው አስተዋጽኦ እጅግ በጣም እየጨመረ መጥቷል

የድሬዳዋ ነጻ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## የዋጋ ንረቱን የማረጋጋት ትልም እንዴት ይሳካል?

ፋንታነሽ ክንዴ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረቱን ለመቀነስ የተወሰዱ የገንዘብ ፖሊሲ የማሻሻያ ርምጃዎች ተጨባጭ ውጤት እያስገኙ መሆኑን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምህረቱ የባንኩን የ2016 የሩብ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት

የዋጋ ንረቱን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## "ኢትዮጵያ ስጠየቀችን ጥያቄ መልስ መስጠት ያለብን ጊዜ አሁን ነው"

- ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ

አዲሱ ገረመው



ፎቶ በአሸናፊ ጉደታ

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ ኢትዮጵያ ለጠየቀችን ጥያቄ መልስ መስጠት ያለብን ጊዜ አሁን ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው ገለጹ።

ፕሮፌሰር ዳንኤል የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ለማማከር የተሰየመውን "አማካሪ ኮሚቴ" የሥራ ተነሳሽነትና ዝግጁነትን አስመልክተው ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ "ሀገራችን ኢትዮጵያ አስተምራናለች። ያለን ሁሉ የሀገራችን ነው። ስለዚህ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን ብለዋል።

ሁሉም የኮሚቴ አባል ለዚህ ቁርጠኛ ነው መሆኑን የጠቀሱት ፕሮፌሰር ዳንኤል፤ የኮሚቴው አባላት ጥሩ ልምድ ያላቸውና አንጋፋ ሰዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ይህን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ኢትዮጵያ

"ኢትዮጵያ ስጠየቀችን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ኢንዱስትሪ ፓርኩ

ለ100 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም አለው

ገጽ 6
















ዜና

# በሀረሪ

## አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ሳስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሠጥቷል

ራስወርቅ ሙሉጌታ

አዲስ አበባ፡- በሀረሪ ክልል በተያዘው ዓመት ሦስት ወራት ውስጥ በ26 የኢንቨስትመንት መስኮች ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ሥራ መግባታቸው ተገለጸ።

በክልሉ የኢንቨስትመንት ቢሮ ዳይሬክተር አቶ ሰሚር ሬድዋን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት 24 ባለሀብቶችን ለማስተናገድ ታቅዶ ለ26 ባለሀብቶች ፈቃድ መስጠት ተችሏል።

እንደ አቶ ሰሚር ገለፃ፣ በእቅዱ ባለሀብቶቹ ከ350 ሚሊዮን ብር በላይ ያስመዘግባሉ ተብሎ የተጠበቀ ቢሆንም ከእቅዱ በላይ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር አስመዝግበው ወደ ሥራ ገብተዋል። ባለሀብቶቹ በማኑፋክቸሪንግ፣ በሆቴል፣ ጤና እና ትምህርት ባሉ የአገልግሎት ዘርፎች ተሠማርተዋል።

በኢንቨስትመንቶቹ ከአንድ ሺህ በላይ ቋሚ እንዲሁም በግንባታ ወቅት ከሁለት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥሩ መሆኑን ኃላፊው አያይዘው ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በነበረው ሂደት በከፍተኛ የገንዘብ መጠን ለኢንቨስትመንት ተመዝግበው ወደ ሥራ ያልገቡ ባለሀብቶች የነበሩ መሆናቸውን ተናግረዋል። አንዳንዶችም ለኢንቨስትመንት በሚል የተሰጣቸውን መሬት እየሸነሸኑ እስከመሸጥ ደርሰው ነበር ያሉት ኃላፊው፤ በመሆኑም ካለፈው ዓመት ጀምሮ መሥራት የሚችሉትን ለመለየት ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ተሠጥቷቸው ወደ ሥራ ያልገቡ ስምንት ኢንቨስተሮች ፈቃዳቸው መነጠቁን አቶ ሰሚር ጠቁመዋል።

በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች የተሠማሩ 37 ባለሀብቶችም ማስጠንቀቂያ ተሠጥቷቸው ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል ብለዋል። ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው በሚጠበቀው ደረጃ ወደሥራ ካልገቡ ተመሳሳይ ርምጃ የሚወሰድባቸው ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል።

በክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ የዳያስፖራዎች ተሳትፎ አበረታች እንደሆነ የተናገሩት አቶ ሰሚር፤ ነገር ግን ከከተማ ኢንቨስትመንት ባለፈ በተለያየ መስክ መሳተፍ የሚፈልጉ የክልሉ ተወላጆች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በመሆኑም በኢንቨስትመንት ቢሮው በኩል በደቡብ፤ በኦሮሚያ፤ በአፋርና ሌሎች ክልሎችም በሚፈልጉት ዘርፍ እንዲሠማሩ ሁኔታዎች እየተመቻቹላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ ለቀጣይም ከተማዋ በኢትዮጵያ የከተማ ኢኮኖሚ ካላቸው ሶስት ከተሞች አንዷና የቱሪዝም ማእከል እንደመሆኗ በአገልግሎት ዘርፍ የበለጠ ትኩረት ተሠጥቶ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

በተጨማሪ አዳዲስ ለሚመጡ ባለሀብቶች ቦታና ሌሎች አገልግሎቶችን ከማቅረብ ባለፈ ቢሮው ከባንክ ጋር በማገናኘት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

# ወንጂ ስኳር

## ፋብሪካ አንድ ሚሊዮን ኩንታል ሥኳር ለማምረት ዝግጅት እያደረገ ነው

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የወንጂ ስኳር ፋብሪካ በ2017 የምርት ዘመን 1 ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ለማምረት የሚያስችለውን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አማን አስታወቁ፡፡ ፋብሪካው በ2016 የምርት ዘመን 327 ሺህ ኩንታል ስኳር ያመርታል፡፡

የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአገዳ ምርታማነት መቀነስ፣ የተፋሰስ ችግር፣ የማሽነሪዎች አለመታደስ፣ የማሽነሪ መለዋወጫ እቃ እጥረትና የውጭ ምንዛሬ እጥረት የፋብሪካው ችግሮች ናቸው፡፡ ችግሮቹም ፋብሪካው የአቅሙን 30 በመቶ ብቻ እንዲሠራ አድርገውት ቆይተዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ፋብሪካው ያሉበትን ችግሮች በመቅረፍ በመጪው የ2017 በጀት ዓመት አንድ ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ለማምረት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። እቅዱን ለማሳካት የሸንኮራ አገዳ ሽፋንን ማሳደግና የማሽነሪዎች እድሳት ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡


የአገዳ ሽፋንን የማስፋት ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ጀማል፤ አሁን ስምንት ሺህ 200 ሄክታር መሬት በሸንኮራ አገዳ ምርት ተሸፍኗል ብለዋል።

በተጨማሪም የፋብሪካው መሠረተ ልማቶች 70 ዓመት ያስቆጠሩ በመሆናቸው በተሠራ የማሻሻያ ሥራ መሠረት ውጤቶች እየተገኙ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም በ2017 አንድ ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ለማምረት የያዘውን እቅድ እውን እንደሚያደርገው ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ ለመሥራት 14 ሺህ 500 ሄክታር መሬት የሚያስፈልገው መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ በዓመት እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ማምረት አቅም አለው። ፋብሪካው በታሪኩ በ2007 ዓ.ም 12 ሺህ 367 ሄክታር መሬት በሸንኮራ አገዳ በመሸፈን 1 ሚሊዮን 158 ሺህ ኩንታል ስኳር ማምረት ችሏል፡፡ በቀጣይ ወደ ነበረበት ታሪክ እንዲመለስ መሠረታዊ የማሻሻያ ሥራዎች እንደሚሠሩ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በ2016 የምርት ዘመን ያለው የሸንኮራ አገዳ ምርት በቀጣይ አራት ወራት ብቻ ስኳር ለማምረት የሚውል ነው፡፡ ይህም 327 ሺህ ኩንታል ስኳር ለማምረት ይውላል፡፡

የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከ1946 ዓ.ም ጀምሮ ስኳር ማምረት ላይ የሚገኝ ግንባር ቀደም ፋብሪካ ነው። እንዲሁም 31 ዋት ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚችል ፋብሪካ ነው። ይሁንና በዘርፈ ብዙ ችግሮች በአሁኑ ጊዜ በዓመት ከ 3 እስከ 4 መቶ ሺህ ኩንታል ስኳር ብቻ እያመረተ ይገኛል፡፡



አቶ ጀማል አማን



# በመዲናዋ ከ49 ሺህ በላይ ይዞታዎችን ወሰን የማካለልና የቅየሳ ሥራ ተሠርቷል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ በሶስት ወራት ውስጥ 49 ሺህ 384 ይዞታዎችን የወሰን ማካለልና ቅየሳ ማከናወኑን አስታወቀ።

በኤጀንሲው የእቅድና በጀት ዝግጅት ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ተወካይ አቶ ቢንያም አከለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው ዓመት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት የእወጃ ሥራ ተካሂዷል።

በተካሄደው እወጃ አሠራሩን እና አገልግሎት አሠጣጡን ግልጽ ለማድረግ ከአንድ ሺህ በላይ የሕዝብ ታዛቢዎችንና ቅሬታ ሰሚ የማስመረጥና ግንዛቤ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

በዚህም 49 ሺህ 384 ይዞታዎችን የወሰን ማካለልና የቅየሳ ሥራ ተከናውኗል ያሉት አቶ ቢንያም፤ ይዞታ ማረጋገጥ ሥራው የተሳካ እንዲሆን ባሉት ክፍለ ከተሞች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራቱን አብራርተዋል።

ለ20 ሺህ 514 የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል ያሉት አቶ ቢንያም፤ ይህ የተደረገው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራው በሕዝብ ተሳትፎ የታጀበና የተሳካ ለማድረግ መሆኑን ጠቁመዋል። በዚህም የይረጋገጥልኝ ማመልከቻዎች በአግባቡ መስተናገድ ችለዋል ሲሉ ነው የተናገሩት።

ተገልጋዮችን በሚያንገላቱ እና የአሠራርና የሕግ ጥሰት በፈፀሙ 16 አመራርና ባለሙያዎች ላይ ዕርምጃ መወሰዱን አቶ ቢንያም ገልጸዋል።

አቶ ቢኒያም እንደገለጹት፤ በሩብ ዓመቱ አንድ ሺህ 75 ፋይሎች በአምስት ክፍለ ከተሞች ተፈትሸዋል። ከነዚህም ውስጥ 776 የአሠራርና የሕግ ክፍተት ተገኝቶባቸዋል። ቀሪዎቹ 299 ፋይሎች በሕግና በመመሪያ መሠረት ትክክል መሆናቸውን በማረጋገጥ በተገኙት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ ርምጃዎች ተወስዷል።

ኤጀንሲው በሚያከናውነው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ፣ የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን ማደራጀትና የአድራሻ ሥርዓትን ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህም አጋር አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ከ 11 ተቋማት ጋር የቅንጅታዊ ትስስር መፍጠር ተችሏል ሲሉም ገልጸዋል።

የእወጃ ሥራው በተያዘለት የጊዜ ገደብ መጠናቀቁ በሶስት ወራት ውስጥ እንደ ጥንካሬ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው ያሉት አቶ ቢኒያም፤ የሲስተም መቆራረጥ፣ የግብዓት ችግሮች እና የሰው ኃይል ዕጥረት የነበሩ ክፍቶች ነበሩ ሲሉ አብራርተዋል።

# ባለፉት አምስት ወራት ከ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በወባ በሽታ ተይዘዋል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት ከ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በወባ በሽታ መያዛቸውን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ወረርሽኙን ለመከላል በሁለት ዓመት ውስጥ ከ20 ሚሊዮን በላይ አጎበሮች ተሠራጭተዋል፡፡

በጤና ሚኒስቴር በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር የወባና ሌሎች ትንኝ ወለድ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዴስክ ኃላፊ አቶ ጉዲሳ አሰፋ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በጀት ዓመቱ አምስት ወራት ለ4 ሚሊዮን 587 ሺህ 495 የወባ ተጠርጣሪ ህሙማን ምርመራ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከነዚህም ውስጥ 1 ሚሊዮን 575 ሺህ 442 የወባ ህሙማን ሆነው በመገኘታቸው አስፈላጊውን ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል፡፡

አቶ ጉዲሳ እንደገለጹት፤ እየጨመረ የመጣውን የወባ ወረርሽኝ ለመከላከል በሁለት ዓመት ውስጥ ከ20 ሚሊዮን በላይ አጎበሮች ማሠራጨት ተችሏል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት እስካሁን ባለው ጊዜ ከ330 ሺህ በላይ አጎበሮችን ለክልሎች ከማሠራጨት በተጨማሪ፤ 1 ሚሊዮን 504 ሺህ 739 ቤቶች የወባ ትንኝ መከላከያ ኬሚካል እንዲረጩ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ከስድስት ሺህ በላይ ባለ 5 ሊትር ፀረ-እጭ ኬሚካል ወደ ሁሉም ክልሎች ተሠራጭቶ ቋሚ የወባ መራቢያ ቦታዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ርጭት መካሄዱንም አስረድተዋል፡፡

ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በሽታው ባልተጠበቀ መልኩ እየጨመረ መሄዱን የገለጹት አቶ ጉዲሳ፤ 75 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ አካባቢዎች ለወባ በሽታ ስርጭት አመቺ በመሆኑ 69 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ተጋላጭ ነው ብለዋል፡፡

በተለይም የአማራ እና የኦሮሚያ ክልሎች ትልቁን ድርሻ የሚይዙ ቢሆንም በደቡብ ምዕራብ ክልል፣ በደቡብ ክልል እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በስፋት የሚስተዋል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በአየር ንብረት ለውጥና የዝናብ መቆራረጥ ምክንያት የወንዞች መቆራረጥ፣ የድርቅና ጎርፍ መከሰት፣ በየአካባቢው ያቆረ ውሃ መኖር፣ የፀጥታ ችግር ጋር ተያይዞ አገልግሎቶችን ለመስጠት አስቸጋሪ መሆን ለበሽታው መጨመር በዋነኝነት ይጠቀሳሉ ብለዋል፡፡

የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ጨምሮ የወባ መመርመሪያና የፀረ-ወባ መድኃኒቶችን በሁሉም ጤና ተቋማት በበቂ መጠንና ዓይነት እንዲኖር የማድረግ፣ ያልተሰራጩ አጎበሮችን የማድረስ፣ የወባ አስተላላፊ ትንኝ እንዳትራባ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን የማፋሰስና የመደልደል ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የወባ መከላከልና ቁጥጥር ስልቶችን በተጠናከረ መንገድ ለመሥራትና ወደ ነበረበት ለመመለስ አዲስ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በዚህም የወባ በሽታ መከላከል፣ መቆጣጠርና የማጥፋት ስልቶችን በሁሉም ደረጃ በኃላፊነትና በተጠያቂነት እንዲሠሩ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች ይሠራል ብለዋል፡፡



አቶ ጉዲሳ አሰፋ



# ክልሉ ከቱሪዝም መዳረሻዎች መግቢያ ክፍያ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ከቱሪዝም መዳረሻዎች መግቢያ ክፍያ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን የአፋር ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

በአፋር ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመርያ ሩብ ዓመት 900 የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን አስተናግዷል። በዚህም ከቱሪዝም መዳረሻዎች የመግቢያ ክፍያ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱንም አስታውቋል።

በ2016 በጀት ዓመት 3 ሺህ የውጭ አገር ጎብኚዎችን ለማስተናገድ አቅዶ ሲሠራ መቆየቱን ኃላፊው አንስተዋል።

ክልሉ ላይ ያለው የሰላም ሁኔታ መጠናከር፣ የቱሪዝም መዳረሻዎች መጨመርና መሠረተ ልማቶች መሻሻል ወደ ክልሉ የሚመጡ ጎብኚዎች ቁጥር እንዲጨምር ማስቻሉን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ከውጭ ሀገር ጎብኚዎች ባለፈ በርካታ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችም ክልሉን እየጎበኙ ነው ብለዋል።

በመሆኑም ቢሮው ከጎብኚዎች መግቢያ ክፍያ ካገኘው አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ባለፈ ለአስጎብኚዎች የሚከፈል ክፍያ፣ መኪና ኪራይ፣ የሆቴልና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያን ጨምሮ ጎብኚዎች ክልሉ ላይ በሚቆዩበት ጊዜ በርካታ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ክልሉ ያለውን የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ መስህቦች የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይነትም በተለያዩ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫሎች ከመሳተፍ ጀምሮ ያሉ መድረኮችን ሁሉ አሟጦ ለመጠቀም እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል።

ባለፉት ዓመታት ክልሉ ላይ ተፈጥሮ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የጎብኚዎች መቀዛቀዝ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ያለው የጎብኚዎች ፍሰት ከታቀደውም በላይ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው፤ ይህ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ጎብኚዎችም በቆይታቸው ደስተኛ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

አስጎብኚዎችን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ዜጎችን የማሠልጠንና የማደራጀት ሥራም እየተሠራ ነው ብለዋል።

ለቱሪስት መዳረሻ ይሆናሉ ተብለው የተዘጋጁ አምስት ካርታዎች መኖራቸውን የጠቀሱት አቶ አሕመድ፤ በእነዚህ ሥራዎች የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ላይ የግል ባለሀብቱ በስፋት እንዲሳተፍ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሆነም አስታውቀዋል።

ቢሮውምመዳረሻዎችንየማስተዋወቅሥራከመሥራት ባሻገር የግል ባለሀብቱና ግለሰቦች ያልገቡባቸውን የሥራ መስኮች ወደ ሥራ በማስገባት ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ማሳያ ለማድረግና ጎብኚዎችን ቆይታ ሊያራዝሙ የሚችሉ ምቹ መሠረተ ልማቶችን ለመገንባት ትኩረት ተሠጥቶ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአፋር ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በ2015 በጀት ዓመት ከቱሪዝም መዳረሻዎች መግቢያ ክፍያ ያገኘው አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር እንደነበር ታውቋል።

# ባለሥልጣኑ ብልሹ አሠራርንና ኢፍትሃዊ ርምጃ አወሳሰድን ለማስቀረት እየሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በደንብ ማስከበር አገልግሎት ላይ የሚስተዋሉ የሌብነት፣ የብልሹ አሠራርና ፍትሕዊ ያልሆነ ርምጃ አወሳሰድ ችግሮችን ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ የሠላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ እንደገለጹት፤ በደንብ ማስከበር አገልግሎት ላይ የሚስተዋሉ የሌብነት፣ የብልሹ አሠራርና ፍትሕዊ ያልሆነ ርምጃ አወሳሰድ ችግሮች ይታያሉ። እነዚህን ችግሮች በመፍታት ለማህበረሰቡ ፍትሕዊ አገልግሎት ለመስጠት ውስጥን የማጣራት ሥራ እየተሠራ ነው።



ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ

ማህበረሰቡ በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ደንብ ማስከበር አሠራር ላይ የሚስተዋሉ የሌብነት፣ የብልሹ አሠራርና ፍትሕዊ ያልሆነ ርምጃ አወሳሰድ ችግሮች እንዳሉ በተደጋጋሚ እንደሚያነሳ ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

በደንብ ማስከበር ሥራ ማህበረሰቡ እያነሳቸው ያሉ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ፈትቶ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት እየሠራን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከአገልግሎቱ አንዳንድ ሠራተኞች ህብረተሰቡ ላይ በብልሹ አሠራር የታጠረ ርምጃ የመውሰድ አሠራርን የሚከተሉ እንዳሉ ጠቅሰዋል።

የሕግ ጥሰትን በሚፈፅሙ ሠራተኞች ላይ ርምጃ በመውሰድ ማህበረሰቡ ላይ እየተፈፀመ ያለውን የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ለመቅረፍ በስፋት እየተከሄደበት ነው ብለዋል።

ወንጀሉን ፈፅመው በተገኙ አካላት ላይም ርምጃ እየተወሰደባቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ ተቋሙ እየሠራ ያለው ደንብንና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሆኑን ተናግረዋል።



ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጁ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በበኩላቸው፤ የሌብነትና የብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

በመዲናዋ እየተሠራ ባለው ደንብ የማስከበር ሥራ ውስጥ አልፎ አልፎ የሚታይ ሌብነትና ብልሹ አሠራር እንዳለ ጠቁመዋል።

በሌብነትና ብልሹ አሠራር የተሳተፉ አመራሮችና ሠራተኞች ላይም ርምጃ እየተወሰዳባቸው ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ እስካሁን ባለው ጊዜ 17 በሚደርሱ አመራሮችና ሠራተኞች ላይ ርምጃ እንደተወሰደባቸው ገልጸዋል።

ማህበረሰቡ የሚያነሳቸውን የሌብነት፣ ፍትሕዊ ያልሆነ ርምጃ አወሳሰድና ብልሹ አሠራርን ችግሮች በመቅረፍ መልካም አስተዳደርንና ቀልጣፋ አግልግሎት አሰጣጥን ለመዘርጋት ውስጥን የማጥራት ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ አያይዘውም፤ ከጎዳና ንግድ፣ ደንብና ሥርዓትን ከሚተላለፉ ሰዎች የሚሰበሰብ ሀብት ለመንግሥት ገቢ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በተሠራውም ሥራ በ2015 በጀት ዓመት 34 ሚሊዮን ብር ገቢ የተደረገ መሆኑን ተናግረው፤ በ2016 በጀት ዓመት በሩብ ዓመት አፈፃጸም ሦስት ሚሊዮን ብር ገቢ መደረጉን አብራርተዋል።

ተቋሙ በመዲናዋ እየተሠራ ያለውን ደንብ የማስከበር ሥራ ከማህበረሰቡ ጋር በመቀናጀት አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አትሌቲክሱን ከጥፋት የሚታደግ አፋጣኝ መፍትሔ ያስፈልጋል!

ኢትዮጵያ የዕንቁ አትሌቶች ምድር መሆኗ ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ነው። ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አትሌቶቻቸውን "ዕንቁ" ብለው የሚጠሯቸውም በምክንያት እንጂ በከንቱ ሙገሳ አይደለም። ከጀግናውና ታሪካዊው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ የኦሊምፒክ ማራቶን የባዶ እግር ገድል አንስቶ እስካሁኖቹ ኮከቦች ድረስ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከሌሎች የሚለዩባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ።

በአስቸጋሪና ፈታኝ የሕይወት ውጣ ውረዶች አልፈው ሁሌም ለሀገራቸው ክብር በጀግንነት መዋደቅና ሰንደቃቸውን በዓለም አደባባይ ከፍ ለማድረግ እልህ አስጨራሽ ትግል ማድረጋቸው አንዱ መገለጫቸው ነው። በዚህም ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ዓለም አክብሯቸዋል።

እልፍ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ባልሸነፍ ባይነት ባሕላቸው ለማመን የሚከብዱ ዘመን ተሻጋሪ ስኬቶቻቸውን ያስመዘገቡት የስፖርቱ ዓለም የሚፈቅዳቸውን ሕግጋት አክብረው በንፁሕ የፉክክር መድረክ ነው። ይህም ልዩ መገለጫቸው ሆኖ ቆይቷል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ይህን ሁሉ አኩሪ ታሪክ፣ ገድልና ስኬትን የሚንድ አንድ አደጋ በኢትዮጵያ የአትሌቲክስ መንደር እየተስተዋለ ይገኛል።

ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት የበርካታ ሀገራት አትሌቶች የስፖርቱ ነቀርሳ እየሆነ በሚገኘው የአበረታች ንጥረነገሮች (ዶፒንግ) ተጠቃሚነት ሲታመስ ቆይቷል። በዚህም ኦሊምፒክን በመሳሰሉ ታላላቅ መድረኮች እስከመታገድ የደረሱ ሀገራት አሉ። ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ከዓለም አቀፉ ፀረ አበረታች መድኃኒት ተቆጣጣሪ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባት ምክረሃሳብ ከመቀበል የዘለለ ስጋት ያለባት ሀገር አልነበረችም። አሁን ግን በፍጥነት ነገሮች እየተቀያየሩ መጥተዋል። ችግሩ አፍጥጦ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን "ከቁጥጥሬ ውጪ ነው" እስከማለት ደርሷል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአበረታች መድኃኒቶች ተጠቃሚነት አልፎ አልፎ ቅጣት የተጣለባቸው አትሌቶች ቢኖሩም ትልቅ ስም ያላቸው አይደሉም። ሰሞኑን በዚህ ቅሌት ውስጥ አሉ ከተባሉ አስር አትሌቶች መካከል ግን ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች የወከሉ ጭምር ይገኙበታል። ይህም ችግሩ ምን ያህል ስር እንደሰደደ ያመላከተ ሲሆን ኢትዮጵያም ጉዳዩን በሚቆጣጠረው ዓለም አቀፍ ተቋም ቀይ መብራት ከበራባቸው ሀገራት አንዷ አድርጓታል።

ለዚህ ችግር መባባስ ብዙ ምክንያቶች ቢመዘዙም የአትሌት ወኪሎች (ኤጀንቶች) ሚና ትልቅ መሆኑ ይነገራል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው የአትሌት ወኪሎች 23 ብቻ ናቸው። ሕገወጦቹ ግን ከ300 በላይ ደርሰዋል ሲባል ይሰማል። እነዚህ ግለሰቦች ያለመኖሪያ እና የሥራ ፈቃድ እንደልባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ሲሆን በየጫካው እየዞሩ አትሌቶቻችንን እየበረዙ ነው ሲባልም ይደመጣል። እነዚህ ግለሰቦች በአውሮፕላን ጉዞ ያለውን ቁጥጥር ፍራቻ ከጎረቤት ሀገራት በብዛት በመኪና የሚገቡ መሆቻው መባሉ ደግሞ ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ አድርጎታል።

በተጨማሪም ሙያው ከሚፈቅደው ሕግ ውጭ አንዳንድ የመድኃኒት መደብሮችና የጤና ባለሙያዎች መድኃኒቱን እንደፈለጉ እያቀረቡ ይገኛሉ። አትሌቶች ልምምድ በሚሠሩባቸው ቦታዎች ለዚሁ ዓላማ የሚከፈቱ በመሆኑም የችግሩ ስፋት የከፋ አድርጎታል።

በኤሽያና በተለያዩ ሀገራት የሚወዳደሩ አትሌቶች በጉዳዩ እየተጠረጠሩ በመሆኑ ኢትዮጵያን ጥርስ አስነክሶባታል። ይህን ችግር በብዛት ጎትተው እያመጡ የሚገኙት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በማይቆጣጠረው መንገድ በቱሪስት ቪዛና በንግድ ቪዛ ከአገር እየወጡ ውድድሮችን የሚያደርጉ አትሌቶች ናቸው የሚል መረጃ ይነገራል።

እነዚህ አትሌቶች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወይም በጥቅም ተደልለው በዚህ ቅሌት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ላይ እያደረሱ የሚገኙትን ውድመት ቆም ብለው ሊያስቡና ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። አትሌቲክስ የኢትዮጵያ አንድ ዓይን ነው። አንድ ዓይን ያለው ደግሞ በአፈር አይጫወትም። በዚህ ጉዳይ ላይ ቀልድ የለም።

ለግል ጥቅም ሲባል የሚጠፋ ነገር መኖር የለበትም። ይህ የእነ አበበ ቢቂላ፣ ምሩፅ ይፍጠር፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለና ሌሎችም እልፍ የተከበሩ ጀግኖች አትሌቶች ሀገር ነው።

አትሌቶችም ይሁኑ ወኪሎች ለግል ጥቅም የሚጓዙበት አቋራጭ መንገድ አያሌ ጀግኖች በከፍተኛ መስዋዕትነት በዘመናት የትውልድ ቅብብል የገነቡትን ታሪክ፣ ዝናና የሀገር ክብር እንደሚንድ ሊገነዘቡ ይገባል።

ይህን አሳሳቢ ችግር ለመቆጣጠር ኢትዮጵያ እስከ እስር የሚያደርስ ሕግ ብታወጣም አፈፃፀሙ ግን አመርቂ አይደለም። በዚህ ቅሌት ውስጥ የተገኙ አካላት ሕግ ፊት ቀርበው የሚቀጡበት አጋጣሚ እየታየ አለመሆኑ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። እዚህ ላይ ሕግ አስፈፃሚው አካል ቆም ብሎ ነገሮችን መፈተሽ ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን ለአትሌቶች ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ የአበረታች መድኃኒቶች ተጠቃሚነት ጉዳይ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት እስከማድረግ ጥረት አድርጓል። ችግሩ ግን ከግንዛቤና ካለማወቅም የተሻገረ በመሆኑ መንግሥት ጭምር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ግድ ይላል።

ከስፖርት አበረታች ቅመሞች ነፃ የሆኑ ጤናማ ስፖርተኞች እንዲፈጠሩና ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ ተወዳድሮ ማሸነፍን ባሕል ለማድረግ በየደረጃው ችግሩን ለመቆጣጠር ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንክሮ መሥራት አለበት። ከፖሊስ በተጨማሪ የደህንነት ተቋማትም ችግሩን እያቀጣጠሉ አትሌቲክሱን ስጋት ላይ የጣሉ አካላት ላይ ክትትል በማድረግ አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አትሌቲክሳችን ወዴት እያመራ ነው?

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ በዓለም ሕዝብ ዘንድ ስሟ ገኖ ከሚጠራባቸው መስኮች ዋነኛው የአትሌቲክስ ስፖርት ነው። ይህ ገናና ስም ዝም ብሎ በዘፈቀደ የተገኘ አይደለም። ከጀግናውና ታሪካዊው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ አንስቶ አያሌ ከዋክብት አትሌቶች ብዙ ፈተናዎችን አልፈው ደምና ነጭ ላባቸውን አፍሰው ባስመዘገቧቸው ሕያው ድሎች የተገኙ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን የምንጊዜም የዓለም ከዋክብት አትሌቶች የተለዩ የስፖርቱ ዓለም ጀግኖች ሆነው የሚከበሩባቸው በርካታ ገፊ ምክንያቶች አሉ። ዘመናዊ ሥልጠና በደረሰበት ሳይደርሱ በብዙ የሕይወት ፈተናዎች አልፈው ባልሸነፍ ባይነት ወኔና ጀግንነት በባዶ እግራቸው ሳይቀር ዘመን የማይሽራቸው ድሎችን ማስመዝገብ መቻላቸው አንዱ ነው።

በሳይንሳዊ ሥልጠናዎች መታገዝ ከጀመሩ ወዲህም የሌላው ዓለም አትሌቶች ተፈጥራዊ ባልሆነ መንገድ ብቃትና አቅምን በሚያሳድጉ ቴክኖሎጂና መድኃኒቶች ታግዘው ፍትሐዊ ባልሆነ ፉክክር በአቋራጭ ድል ለመጨበጥ ሲጣጣሩ ነፃ ሆነው መቆየታቸው ሌላው ገድላቸው ነው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአትሌቲክሱ የቅርብ ተፎካካሪያችን ኬንያ ሳትቀር ከዋክብት አትሌቶቿ በስፖርት የተከለከሉ አበረታች ንጥረ ነገሮችን(ዶፒንግ) ተጠቅመው በመገኘት ሲታመሱ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከዚህ ቅሌት ጋር ስማቸው እምብዛም ሲጠራ አልነበረም።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ይህ አደጋ በኢትዮጵያውያን አትሌቶች ላይም እያንዣበበ መጥቷል። የመነጋገሪያ ርዕሰ ጉዳይም ከሆነ ቆይቷል። ይህ የንፁሕ ስፖርት ነቀርሳ የሆነ አደጋ በኢትዮጵያ በእንጭጩ ባለመቀጨቱ አሁን ላይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት በዚህ ቅሌት ውስጥ የተገኙ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። መድኃኒቱን ተጠቅመው ተገኙ የሚባሉትም ትልቅ ስም ያላቸው አትሌቶች አልነበሩም። አሁን ግን ነገሮች እየተቀየሩ መጥተዋል። ለዚህም ሰሞኑን በዶፒንግ ቅሌት ውስጥ ከተገኙ 10 ያህል አትሌቶች ሀገራችንን በታላላቅ ዓለም አቀፍ መድረኮች የወከሉ ትልቅ ተስፋ የተጣለባቸው ኢትዮጵውያን አትሌቶች መካተታቸው አንዱ ማሳያ ነው ።

ይህም ኢትዮጵያ የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚ በሆኑ አትሌቶች ብዛት «A Category» (ቀይ መብራት) ውስጥ መግባቷን የሚገልፁ አስደንጋጭ ዜና ይዞ መጥቷል። "ይህንን ችግር አስመልክቶ ሰሞኑን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሕክምና ባለሙያዎች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ብዙ ያልተጠበቁ መረጃዎች /ጉዶች/ ወጥተዋል። የአትሌት ኤጀንቶች(ወኪሎች) ለአትሌቶች አበረታች መድኃኒቶች ተጠቃሚነት ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በስፋት ተወስቷል።

በመግለጫው እንደተገለጸው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው የአትሌት ወኪሎች 23 ብቻ ናቸው። ሕገወጦቹ ግን ከ300 በላይ በላይ ደርሰዋል። እነዚህ ወኪሎች ያለመኖሪያ እና የሥራ ፈቃድ እንደልባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ነው፤ በየጫካው/የልምምድ ቦታ ሳይቀር እየተገኙ አትሌቶቻችንን በዶፒንግ እየበረዙ ነው።

ለአትሌቶች ድጋፍ በመስጠት ሽፋን የአትሌቶች ተወካዮች፣ ከውጭ የሚመጡ አሠልጣኞች፣ ደላሎች ነገሩን እያባባሱና ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆን እያደረጉ ነው። የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ባለመሥራታቸው ችግሩ ሰፊና ስር እየሰደደ ሊመጣም ችሏል።

ማንም የውጭ ዜጋ የመኖሪያ ፍቃድ ሳይጠይቅ መድኃኒቶችን ይዞ አትሌቶች ልምምድ በሚሠሩበት ስፍራ ድረስ ዒላማ አድርጎ እንደሚንቀሳቀስ ቀደም ብሎም ሲነገር የነበረ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት የተወሰደ አስተማሪ እርምጃ ባለመኖሩ ችግሩ መቋጫ አላገኘም ።

ሙያው ከሚፈቅደው ሕግ ውጪ አንዳንድ የመድኃኒት መደብሮችና የጤና ባለሙያዎች መድኃኒቱን ባልተገባ መንገድ ከውጪ በማስገባት አትሌቶች ልምምድ በሚሠሩባቸው ቦታዎች ሳይቀር በስፋት እያቀረቡ ነው። ኬንያ በጉዳይ ቀደም ብላ ነቅታ አትሌቲክሷን ከዚህ አደጋ ለመታደግ ከሀገሯ ያባረረቻቸው ደላሎች፣ የአትሌት ተወካዮችና አሠልጣኝ ነን የሚሉ ግለሰቦች ኢትዮጵያን መሸሸጊያ አድርገው አትሌቲክሱን እየመረዙ ይገኛሉ።

ከ100 በላይ የውጭ ሀገር ሰዎች የአውሮፕላን ቁጥጥርን በመፍራት በመኪና ጭምር ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት ይህንን ተግባራቸውን መቀጠላቸው ከላይ የተጠቀሰው ችግር አይነተኛ ማሳያ ነው። ጉዳይ ተባብሶ የቀጠለና ከመሆኑ ጋር በተያያዘ /የሚጠረጠሩ አትሌቶች በመብዛታቸው ዓለም አቀፉ የፀረ አበረታች መድኃኒቶች ባለሥልጣን ኢትዮጵያን ለመቅጣት ትንሽ ምክንያት ብቻ እየጠበቀ እንደሚገኝም የውስጥ ምንጮች ያመለክታሉ ።

በአሁኑ ወቅት በኤሽያና በተለያዩ ሀገራት የሚወዳደሩ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በስፋት እየተጠረጠሩ ነው። በተለይም ፌዴሬሽኑ አትሌቶችን ለውድድር ስለማይልክ በቱሪስት ቪዛና በንግድ ቪዛ እየወጡ ውድድራቸውን የሚያደርጉ አትሌቶች ችግሩን እንዲባባስ ዋነኛ ተጠቃሽ እየሆኑ ነው።

ፌዴሬሽኑ የት እንኳን እንዳሉ የማያውቃቸውና ተወዳድረው ሲያዙ ብቻ የሚያውቅ አትሌቶች መኖራቸው፤ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር ለመፍትሔው ለመምከር እያስገደደው ይገኛል ።

በርግጥ እንደ ሀገር ቀደም ሲል ችግሩን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን ውስጥ የተካተተ ቢሆንም በአግባቡ ሥራ ላይ አለማዋሉ፤ ችግሩን ከሚያባብሱ አካላት ይልቅ የቅጣት እርምጃው አትሌቶች ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑ ለችግሩ መባባስ አንዱ ምክንያት እንደሆነም የሚያነሱ አሉ ።

ችግሩ ኢትዮጵያ የምትታወቅበትን የንጹሕ አትሌቲክስ ስም የሚያጠለሽ ስለሆነ ምንም ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። አጓጊ ሽልማቶችና ከጥቅማ ጥቅም ጋር በተያያዘ ጥቂት አትሌቶች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሚሠሩት ስህተት እልፍ ጀግኖች የገነቡትን የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ክብርና ዝና እንዳይንደው ቆም ብሎ ማሰብ ይጠበቅብናል።

ጉዳዩ እየሞቀና እየበረደ ስር ወደ መስደድ እየተጓዘ በመሆኑ ትክክለኛ ባለቤት ኖሮት እልባት ማግኘት ይኖርበታል። ችግሩ ከአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ቁጥጥር በላይ በመሆኑም ጉዳዩን በበላይነት የሚመራ ሀገራዊ ኮሚቴ ሊቋቋም ይገባል።

አበረታች መድኃኒት የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ስጋት ውስጥ የከተተ በመሆኑ አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድና ከስሩ ነቅሎ ለመጣል የብዙ ባለድርሻ አካላት ርብርብን እንደሚጠይቅ ታውቆ አስቸኳይ የባለድርሻ አካላት ስብሳባ መጠራቱ ጥሩ ጅምር ነው። አንድ መፍትሔ ይዞ እንዲመጣም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ አፋጣኝ ርምጃዎችን እንደ ሀገር መውሰድ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው።

የዶፒንግ የሕግ ጥሰቶችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 526 ላይ የተደነገገውን ተግባራዊ ለማድረግና በቀጣይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን የክትትልና ቁጥጥር ሥራ በየእርከኑ አጠናክሮ ማስቀጠል ለነገ የሚባል ሥራ መሆን የለበትም። መንግሥት በፖሊስና በደህንነት ተቋማት ለችግሩ ተጋላጭ የሆኑ ስፍራዎችን በመለየት በጥብቅ ክትትል በወንጀሉ እየተሳተፉ የሚገኙ ግለሰቦችና ፋርማሲዎችን አድኖ የማያዳግም እርምጃ ሊወስድ ይገባል።

በውድድር የሚሳተፉ ስፖርተኞችም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የችግሩ ሰለባ እንዳይሆኑ ለእያንዳንዷ ጥቃቅን ነገር ጥንቃቄ ሊለያቸው አይገባም። የቀደምት አትሌቶችን ፈለግ በመከተል በአሠልጣኞቻቸው የሚሰጣቸውን ሥልጠና በመቀበል እና የተፈጥሮ አቅማቸውን በመጠቀም ስፖርቱን ሊከውኑ ይገባል ።

አበረታች ቅመሞች በመጠቀም ለማሸነፍ መሞከር ውጤቱ ጊዜያዊ ነው። ተፈጥሯዊ ውጤት አይደለም። አንድ ቀን ውርደት ያስከትላል። ጉዳቱ የግለሰብ ብቻ ሳይሆን እንደሀገርም በገንዘብ የማይተመን ጥፋት እንደሚያመጣ ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም።

ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባቸዋል። የፀረ-ዶፒንግ ጉዳይ በመዋቅራችው ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ማድረግ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። እንደ አገር በባለሥልጣን ደረጃ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ፀረ አበረታች መድኃኒቶች ተቋም ችግሩን ለመፍታት የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ።

# ኢንዱስትሪ ፓርኩ ለ100 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም አለው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ፓርኩ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ 100 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥር የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ::

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሥራ አስኪያጅ ሰናይት መብሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ 80 በመቶ የሆነውን ኢኮኖሚ በግብርናና የሚሸፈን ነው::

ሆኖም የሚመረተው ምርት በባህላዊ መንገድ ተመርቶ እና ምንም እሴት ሳይጨመርበት ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ እየቀረበ ይገኛል::

እዚህ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሚናቸው ትልቅ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጇ፤ ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ የገበሬውን ምርት በቀጥታ ወደ ተጠቃሚው ከማድረስ ባለፈ እሴት ጨምሮ በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባል ብለዋል::

ይህም ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ከመተካት ባለፈ የውጭ ምንዛሬን ለማምጣት ትልቅ ሚና እንደሚኖረው አብራርተዋል::

እንደ ወይዘሮ ሰናይት ገለፃ፤ በአሁኑ ጊዜ 30 የሚሆኑ ባለሀብቶች ኢንደስትሪ ፓርኩ ውስጥ ለመስራት ውል ገብተዋል:: አንድ የማር ማቀነባበሪያ ፋብሪካም ሥራ ጀምሯል::

በፓርኩ ውል የገቡት ባለሀብቶች ሁሉም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የጠቀሱት ኃላፊዋ፤ የሚጠቀሙት ግብዓት በሀገር ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ በፓርኩ ውስጥ መሥራት ለሚፈልግ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ቅድሚያ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ አብራርተዋል::

የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ሥራ አስኪያጅ አደም አብዱራህማን በበኩላቸው፤ ኢንዱስትሪው የግብርና ምርቶችን እያቀነባበረና እሴትን እየጨመረ የሚያመርት መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህም 90 በመቶ የሚሆነው ምርት ወደ ውጭ ይልካል ብለዋል::

ኢንዱስትሪው አትክልትና ፍራፍሬ፣ ቡናና ቅመማ ቅመም፣ ጥራጥሬዎች፣ ሥጋ፣ ሰብል እና ማር የሚያቀነባብር ሲሆን ፓርኩ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ 100 ትላልቅ ባለሀብቶችን በመያዝ 100 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ይችላል ብለዋል::

እስካሁን ተዋውለው በገቡ ባለሀብቶችም 11 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፈጠሩን አብራርተዋል::

ፓርኩ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች ሁሉ የተሟላለት መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ ባለሀብቶች በፓርኩ ማልማት እንዲችሉ የኦሮሚያ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የተለያዩ ሥራዎች እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል::

# የዋጋ ንረቱን የማረጋጋት ትልም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን በጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ሲያቀርቡ፤ ተለዋዋጭ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ መቀዛቀዝ መፍጠሩ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ጫና ማሳደሩን ገልጸዋል።

ለጋሽ ሀገራት ለታዳጊ ሀገራት ይሰጡት የነበረው ብድርና ርዳታ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገራት የዋጋ ንረት እንዲያጋጥማቸው ማድረጉንም አንስተዋል::

እንደ ብሔራዊ ባንክ ገዥው ሪፖርት፤ የዋጋ ንረትን ለመቀነስ የተለያዩ የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያ ርምጃዎችን እየተወሰዱ ነው:: በዚህም ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተዋል:: በዚህም ለወራት ከ30 በመቶ በላይ የነበረውን የዋጋ ንረት በመስከረም ወር ወደ 27 ነጥብ 7 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል:: በተያዘው በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የዋጋ ንረቱን ከ20 በመቶ በታች ለማውረድ እየተሠራ ነው::

በሌላ በኩል የዘርፉ ምሁራን አሁን ላይ የሚስተዋለው የዋጋ ንረት በጊዜ መፍትሔ ማግኘት እንዳለበት እያሳሰቡ ነው::

ለመሆኑ የብሔራዊ ባንክ እቅድ ሊሳካ የሚችል ነው? በሂደቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችና የመፍትሔ ሃሳቦችስ ምን መሆን አለባቸው?

የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪው ፕሮፌሰር አለማየሁ ገዳ እንደሚሉት፤ ግብርናው ምርትና ምርታማነት ከሕዝብ ቁጥር ጋር አለመመጣጠን፣ ተገቢ ያልሆነ የብር ህትመት፣ የብር ዋጋ መርከስና የነጋዴዎች ያልተገባ ትርፍ መፈለግ የዋጋ ንረቱ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው::

ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረቱን ከ20 በመቶ በታች ለማውረድ ማቀዱ መልካም መሆኑን የሚጠቅሱት ፕሮፌሰር አለማየሁ፤ በበርካታ ሀገራት ያለው ልምድ እንደሚያሳየው ባንኮች ከአስፈጻሚው ውሳኔ ነጻ ሆነው አስፈላጊውን ርምጃ ይወስዳሉ:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተደራጀው በአስፈጻሚው ሥር ሆኖ ስለሆነ ከአስፈጻሚው ፍላጎት የተለየ ርምጃ ላይወስድ ይችላል:: ይህ ደግሞ እቅዱን ለማሳካት እንቅፋት ሊፈጥርበት ይችላል ይላሉ::

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የዋጋ ንረቱን ለመቀነስ የአጭር ጊዜና ረጅም ጊዜ ርምጃዎች ያስፈልጋሉ:: የዋጋ ንረቱን እያባባሰው ያለው በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ባሉ አለመረጋጋቶች ምክንያት ምርቶች ስለማይዘዋወሩ ነው:: በመሆኑም በአጭር ጊዜ ሊወሰድ የሚገባው ርምጃ በሁሉም አካባቢ ሰላማዊ ሁኔታን መፍጠር ነው::

የተጀመሩ የእሁድ ገበያዎችን በየአካባቢው ማስፋፋትና መሠረታዊ እቃዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግ ሌላኛው መፍትሄ ነው የሚሉት ባለሙያው፤ ይህም ነጋዴው የሚያግበሰብሰውን ትርፍ እንዲተውና ሸማቾች በተመጣጠነ ዋጋ ምርት እንዲያገኙ ያደርጋል ብለዋል::

የረጅም ጊዜ መፍትሔዎች ሊሆኑ የሚችሉ ግብርናውን ላይ የሚሠሩ ሥራዎችን በዘመቻ ሳይሆን በሳይንሳዊ ዘዴ እንዲመሩና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግ መሆኑን ያመላከቱት ፕሮፌሰር አለማየሁ፤ የሕዝብ ቁጥር እድገት ከኢኮኖሚው እድገት ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን መሥራት ያስፈልጋልም ብለዋል::

የብር ዋጋ እንዲረክስ የውጭ ኃይሎች ጫና እያደረጉ ነው የሚሉት ተመራማሪው፤ መድሃኒት፣ ማዳበሪያ፣ ነዳጅና ሌሎችም በርካታ ምርቶች ከውጭ ይገባሉ:: በመሆኑም ብድር ለማግኘት በሚል የብርን ዋጋ መቀነስ ይዞ ሊመጣ የሚችለውን መዘዝ ማሰብ ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል::

ወደ ሀገር ቤት ሬሚታንስ ለሚልኩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚደረገውን ምንዛሪ ከፍ ማድረግ የተሻለ ውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ሊያግዝ እንደሚችልም ጠቅሰዋል::

የብሔራዊ ባንክ እቅድ እንዲካ የአስፈጻሚው አካል ለባንኩ አስፈላጊውን ነጻነት መስጠትና አላስፈላጊ የብር ሕትመት ማስወገድ ላይ ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል::

ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ እንደሚሉት ደግሞ፤ ዋናው የዋጋ ንረት ምክንያት የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ነው:: በዚህም ምክንያት ለጥቂት እቃዎችና አገልግሎቶች ሰዎች ውድድር ውስጥ ስለሚገቡ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ከፍተኛ ገንዘብ አውጥተው ይገዛሉ::

ብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ፍሰትን ለመቀነስ ጥረት እያደረገ መሆኑን የሚገልጹት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ባንኮች ካላቸው ብድር ካፒታል 14 በመቶ ብቻ እንዲሰጡ ተደርጓል:: ይህ ደግሞ የተቀመጠውን እቅድ ለማሳካት ያግዛል ይላሉ::

የዋጋ ንረት ምጣኔውን ለመቀነስ የአቅርቦትና ፍላጎትን ማጣጣም ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ብዙ ሀገራት ላይ የሸማች ማህበራት ነጋዴዎቹ ላይ ብሎም መንግሥት ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ገበያውን በማረጋጋት በኩል ጉልህ ሚና ይጫወታሉ:: ኢትዮጵያ ውስጥም ገለልተኛ የሆኑና ጠንካራ የሸማች ማህበራት እንዲኖሩ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል::

የብሔራዊ ባንክ እቅድ ለማሳካት ሀገር ውስጥ የሚታየው አለመረጋጋት ዋነኛ ፈተና ሊሆን እንደሚችል የሚጠቅሱት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ሰላምና መረጋጋት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉም አክለዋል::

በተጨማሪም መንግሥት በተለያዩ ምርቶች ላይ የሚያደርጋቸው ድጎማዎች ገበያውን በሚያረጋጋ መልኩ እንዴት ተግባዊ መሆን አለባቸው የሚለውን ማጥናትና ተገቢ ርምጃዎች መውሰድም ይጠይቃል ሲሉ ያስረዳሉ::

የዋጋ ግሽበት ብዙ ሀገራት ላይ የደህንነት ስጋት ሆኗል ያሉት ምሁሩ፤ ኢትዮጵያ ውስጥም አስፈላጊው ርምጃ ተወስዶ የሕዝቡን ጫና ማቃለል ካልተቻለ አስጊ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ሲሉ ጠቁመዋል::

በመሆኑም መንግሥት የጀመራቸው የውጭ ባንኮች መግባት፣ ካፒታል ገበያ መቋቋምና የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው ተሳትፎ መጠናከር የተረጋጋ ገበያ እንዲኖር በማድረግ በኩል ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው መሥራት ያስፈልጋል::

እንደ ባለሙያው ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ሰፊ የሚታረስ መሬት፣ ውሃና 70 በመቶ የሚሆኑት ዜጎችም ወጣቶች ናቸው:: በመሆኑም ወጣቶች ሠርተው ሀብት እንዲያፈሩ የሚያስችሉ ሰፋፊ እርሻዎችን ማቋቋም ያስፈልጋል:: ባንኮችም ትኩረታቸውን ወደ ግብርናው አድርገው ለግብርና የሚሰጡትን ብድር ማሳደግ አለባቸው::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንኩ ገዥ ማሞ ምህረቱ፤ የሀገር ውስጥ የብድር እድገት በ14 በመቶ ጣሪያ እንዲገደብ፣ መንግሥት ለበጀት ጉድለት ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደውን የብድር መጠን በእጅጉ ለመቀነስና ባንኮችም የበጀት ጉድለታቸውን በራሳቸው እንዲሞሉ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የባንኩን ማቋቋሚያ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ማሻሻል የባንኩን ነፃነትና ተጠያቂነት ለማረጋገጥና የተሻለ የአሠራር ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን ገልፀው፤ ይህም ባንኩ ከዓለምና ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም ዘመናዊና ቀልጣፋ አሠራር መዘርጋት ያስችለዋል:: ይህ ደግሞ የተቀመጡ እቅዶችን ለማሳካት የተሻለ ሥራ ለመሥራት ተጨማሪ አቅም ይፈጥርለታል ብለዋል::

እንደ ምሁራኑ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚስተዋለው የዋጋ ንረት በጊዜ መፍትሔ ካላገኘ ሀገሪቱን ችግር ላይ ሊጥል ይችላል:: ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረቱን ለመቀነስ የጀመራቸውን ርምጃዎች አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል::

አስፈጻሚው አካልም ለባንኩ እቅድ መሳካት ከሚያደርገው ድጋፍ ባለፈ ባንኩ ጠንካራ ርምጃዎችን እንዲወስድ ነጻነት መስጠት ያስፈልጋል::

# የድሬዳዋ ነጻ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሚሉት ዶክተር ሙሉጌታ፤ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰቱም እያደገ መጥቷል ብለዋል።

በውስጡ ያሉ ፓርኮችም ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ መግባታቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይ ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት ምቹ ሊያደርጋት የሚችል ትልቅ እድል መሆኑን ያብራራሉ። ከኢንቨስትመንት ፍሰቱ ባሻገር የቱሪዝም ፍሰትን ለመጨመር አወንታዊ ሚና ይኖረዋል ሲሉም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አህጉር አቀፍ የነጻ ንግድ ቀጣና አካል ፈራሚ ሀገር ናት ያሉት መምህሩ፤ ወደ ውድድሩ ይዛ የምትገባውም የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣናን ነው። ይህም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ፋይዳን የሚያጎናጽፍ ይሆናል። እንደ ሀገር በአጭር ጊዜ ለመበልጸግ የሚያግዝ በመሆኑ በሌሎች አካባቢዎች መከፈት እንዳለበት ገልጸዋል።

ዶክተር ሙሉጌታ እንዳሉት፤ ነጻ የንግድ ቀጣናው ያለበት ቦታ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ቅርብ በመሆኑ የንግድ ትስስርን ለማፋጠን ይረዳል። ኢትዮጵያም በተመጣጣኝ ዋጋ ከጎረቤት ሀገራት የተለያዩ ምርቶችን ለማስገባት ያስችላታል። ይህም የዜጎችን የኑሮ ጫና ለማቃለል ይረዳል።

የንግድ ቀጣናው በ2016 በሩብ ዓመት ውስጥ ብቻ አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማስገኘት የቻለበትን ተሞክሮ ማስፋት ከተቻለ፤ በጎረቤት ሀገራት ያለውን ንግድ ከማጠናከር በተጨማሪ የኢኮኖሚ ውህደትን ሊፈጥር የመቻል አቅሙ የጎላ መሆኑንም ዶክተር ሙሉጌታ ገልጸዋል።

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶክተር ዘሪሁን ተምሳስ በበኩላቸው፤ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና መከፈቱ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ትልቅ ሚና እንዳለው ይገልፃሉ።

ነጻ የንግድ ቀጣና ዋና ዓላማ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰትን መሳብ፣ የወጭ ንግድን ማሳደግና ከፍተኛ የሆነ የሥራ እድልን መፍጠር እንዲሁም ጥቅል ምርትን ማሳደግ መሆኑን በማብራራት፤ ነጻ የንግድ ቀጣናው ከጅምሩ ለኢኮኖሚ እገዛ እያደረገ ነው ይላሉ።

ከተጀመረ በአንድ ዓመት ውስጥ ከሁለት ሺህ በላይ የሥራ እድል በመፍጠር ጠቃሚነቱን እያሳየ መሆኑን በማስገንዘብ፤ ወደፊት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የሥራ አጥ ቁጥርን መቀነስ ያስችላታል ብለዋል።

አንዳንድ ሀገራት ከ70 እስከ 90 በመቶ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ከነጻ የንግድ ቀጣናዎቻቸው የሚገኝ ነው። እንዲሁም ለሀገር ፍጆታ የሚውል ምርት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ በነጻ ንግድ ቀጣናዎቻቸው በኩል ያመርታሉ። ወደ ውጭ ይልካሉ። በነጻ የንግድ ቀጣና ታሪክ ውስጥ የሚታወቁ ሀገራት ከ70 እስከ 90 በመቶ፣ 50 በመቶ፣ 35 በመቶ የሚለካ የሥራ እድል መፍጠር ችለዋል።

እንደ ዶክተሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ነጻ የንግድ ቀጣናን መቀላቀሏ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓት እንዲኖራት ያስችላታል። የተቀላጠፈ የወጪና ገቢ ምርት ንግድን እንድታሳልጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በ2016 ሩብ ዓመት ውስጥ ብቻ ከ23 ሚሊዮን ዶላር በላይ የገቢ ምርትን መተካት ችሏል። ከደረቅ ወደቡ በቅርብ ርቀት የሚገኘው ነጻ ንግድ ቀጣናው ከጅቡቲና ከበርበራ ወደብ በቅርበት መገኘቱ ለቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትስስርና ውህደት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

ኢትዮጵያ ነጻ የንግድ ቀጣና ለመተግበር እ.ኤ.አ ከ2020 ጀምሮ በእንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች። ያለምንም የሕግ ማዕቀፍ ወደ ዘርፉ መቀላቀል አደገኛ ነው፤ የሕገወጥ ንግድን ሊያስፋፉ ስለሚችል አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ አሟልቶ ወደ ዘርፉ መግባቱ ከዘርፉ የሚገኘውን ተጠቃሚነት ያሳድገዋል ሲሉም ምሁራኑ አብራርተዋል።

# "ኢትዮጵያ ስጠየቀችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለጠየቀችን ጥያቄ መልስ መስጠት ያለብን ጊዜም አሁን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ ሥራው ሰፊ መሆኑን በመጥቀስ፤ የኮሚሽነሮች ዋና ሥራቸው ሌሎችን ማሠራት ጭምር እንደሆነና ብቻቸውን የ120 ሚሊዮን ሕዝብ ችግር ለመፍታት እያንዳንዱን ሥራ ሠርተው ይጨርሳሉ ብሎ መገመት እንደሚያስቸግር ገልጸዋል። ስለዚህ እነርሱን መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ ምክረ ሃሳብ በማቅረብ እገዛ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

በሚሠሩት ሥራ ተሳታፊዎችን የመለየት ሥነ ዘዴዎችን በማሳየት፤ ሥራው እንዴት መሠራት እንዳለበትና የወደፊት ቀጣይነት ላይ ችግር ሲያጋጥም እንዴት መፈታት እንዳለበት የሚያመላክቱና ሌሎችንም ጉዳዮች በሃሳብ ደረጃ ለማማከር ኮሚቴው ዝግጁ ሆኖ እየሠራ እንዳለ አመላክተዋል።

ኮሚሽኑም ምክረ ሃሳቡን ወስዶ የራሱንም ጨምሮ የማሻሻል ሥራውን ይሠራል ነው ያሉት።

የእኛ ኃላፊነት ምክረ ሃሳብ መስጠት ነው። ትልቁ ሥራ ያለው ግን ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር ነው ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ አማካሪ ኮሚቴው ምክር ይሰጣል እንጂ ለኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጠውን ሥራ እንደማይሠራ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በ1953 ዓ.ም፣ በ1966 ዓ.ም፣ በ1983 ዓ.ም እና በ1997 ዓ.ም የነበሩትን ሀገርን ሊለውጡ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎች አጥታለች ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ እንደ ሀገር በ2010 ዓ.ም የመጣውን መልካም አጋጣሚ ልናጣው አይገባም ብለዋል።

"ይህንን እኛ የምንቆጥረው እንደ አጋጣሚ ብቻ ሳይሆን እንደ መልካም እድል ነው" ሲሉም ሀገራዊ ምክክሩን ገልጸውታል።

ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ሕዝቡ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ወደ ልማት፣ ወደ እድገትና ስምምነት መምጣት እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

እንደ ሀገር ከዚህ ቀደም ከንጉሣዊ አገዛዝ እስከ ኮሚኒዝም የተሞከሩት ሙከራዎች ውጤት አላመጡም ያሉት ፕሮፌሰር ዳንኤል፤ ሠላም ለማምጣት በትብብር አንዱ አንዱን አክብሮ መኖርን አማራጭ የማድረግ ሙከራው እንዲሳካ ማድረግ እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

አማካሪ ኮሚቴው ከዚህ አኳያ ቁርጠኛ ሆኖ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ይሄ አጋጣሚ እንዳያልፈው በቁርጠኛነት እና በልበ ሰፊነት መሥራት አለበት በማለት አሳስበዋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# በክልሉ ለመኸር ወቅት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ለአዝመራው ስብሰባ ትኩረት ተሰጥቷል

**ማሕሌት አብዱል**

ግብርና የምጣኔ ሀብት መሠረቷ ለሆነው ኢትዮጵያ አሁን ያለንበት ወቅት አዝመራ የሚሰበሰብበት ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚጀመርበት ነው። የግብርናው ምርትና ምርታማነት በእጅጉ ለማሳደግ እየተደረገ ባለው ርብርብ ውስጥ ይህ ወቅት ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡

የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየተደረገ ባለው ጥረት እንደ ሀገር ለ2015/16 የምርት ዘመን ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱ ይታወቃል። ለእዚህም ምንም እንኳ በአንዳንድ ክልሎች በማዳበሪያ አቅርቦት ላይ ቅሬታዎች ሲነሱ የነበረ ቢሆንም፣ መንግሥት ለምርት ዘመኑ 21 ቢሊዮን ብር ለማዳበሪያ ግዥ ድጎማ ማድረጉ ይታወሳል።

በምርት ዘመኑ የመኸር ወቅት ብቻ 17 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር የተሸፈነ ሲሆን፣ ይህን ሰብል መሰብሰብ ከተጀመረ ቆይቷል። አሁን ሥራው ተጠናክሮ መቀጠሉን ከግብርና ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

የመኸር ሰብል አሰባሰብ በሀገሪቱ በ2015/16 የምርት ዘመን ወደ 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ነው በዘር የተሸፈነው። በዚህም የእቅዳችን 101 በመቶ መፈጸም ችለናል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው የምርት አሰባሰቡን አስመልክተው በተለይ ለአዲስ ዘመን ሰሞኑን እንዳሉት፤ በተለይ በቆላማ እና ወይና ደጋ አካባቢዎች የደረሱ ሰብሎችን ቶሎ የመሰብሰቡ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በዚህም አሰባሰቡም እስከ ታኅሣሥ አንድ ድረስ ክልሎች በባሕላዊ የአዝመራ አሰባሰብ ወደ ዘጠኝ ነጥብ ስድስት ሄክታር፣ በኮምባይነር ደግሞ ከ844 ሺ 922 ሄክታር በላይ በድምሩ 10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ያለ ሰብል ተሰብስቧል።

ምርት አሰባሰቡም በባሕላዊ መንገድ ከሆነ ተሰብስቦ ተከምሮ ይቆይና ነው የሚወቃው። በኮምባይነር ከሆነ ደግሞ ወዲያው እየተሰበሰበ ይወቃል። ከዚህ አስር ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የአራት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬቱ ሰብል ተውቅቷል። ከዚህም 114 ሚሊዮን 239 ሺ 964 ኩንታል ምርት ተገኝቷል።

አዝመራ የመሰብሰቡ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል ያሉት አቶ ከበደ፣ በባሕላዊ መንገድ ከተሰበሰበው አብዛኛው ገና አልተወቃም፤ ተከምሮ ነው ያለው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አንዳንድ ያልደረሱ ሰብሎች አሉ፤ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር ይችላል፤ ይህንንም ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በሰጠን የአየር ፀባይ ትንበያ መረጃ መሠረት ፀሐያማና ነፋሻማ በሆነ ጊዜ አርሶ አደሩ፣ አመራሩ፣ አጠቃላይ ኅብረተሰቡ፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኛው በቅንጅት ቶሎ የመሰብሰብና ጎተራ የማስገባት ሥራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ በኩል እንዲሠሩ ምክረ ሀሳብ ተሰጥቷል፤ በዚያ መሠረትም እየተሠራ ነው።

ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ፣ ግሪሳና የመሳሰሉትን ተባዮች በመከላከል በኩልም ጉዳት ከመድረሱ በፊት ምክረ ሀሳቦችን ለአርሶ አደሩና ለግብርና ባለሙያው እንዲደርሱ መደረጉን አቶ ከበደ ገልጸዋል። አየሩ ፀሐያማ፣ ደረቃማና ነፋሻማ ሲሆን አርሶ አደሩ ሰብሉን እንዲሰብሰብ ማድረግ ላይ በሚገባ መሠራቱንም ጠቅሰው፣ እስከ አሁን በዝናብ ሳቢያ ሳይሰበሰብ የቀረ፣ ጉዳት የደረሰበት ሰብል አለ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ ነገር እንደሌለም ተናግረዋል።

የአዝመራ መሰብሰቡ ሥራ በክልሎች በተጠናከረ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል። በአማራ ክልልም አዝመራ የመሰብሰቡ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታውቋል። በክልሉ በ2015/16 የምርት ዘመን በመኸር እርሻ አምስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል መሸፈኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አምሳሉ



ጎባው ጠቅሰው፣ ከዚህ ውስጥም 160 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን ይገልጻሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ወቅቱ ምርት የሚሰበሰብበት እንደመሆኑ በክልሉ እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥም በሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚገኝ ሰብል ተሰብስቧል፤ ይህም እንደሚሰበሰብ ከሚጠበቀው ምርት 68 በመቶ ያህል ይሆናል። የምርት አሰባሰብ ሂደቱም በሁለት አይነት መንገድ እየተከናወነ ሲሆን፣ አንደኛው ተለምዷዊ የሆነው ወይም ባሕላዊ መንገድ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ዘመናዊው ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርቱ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው፡፡

> **በክልሉ እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ በሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚገኝ ሰብል ተሰብስቧል፤ ይህም እንደሚሰበሰብ ከሚጠበቀው ምርት 68 በመቶ ያህል ይሆናል**

ተለምዷዊ በሆነው በባሕላዊ መንገድ ሲባል አርሶ አደሩ እርስ በእርስ በመተጋገዝና በመተባበር ምርቱን በጉልበቱ የሚሰበስብበት መንገድ መሆኑን ኃላፊው ጠቅሰው፣ በዘመናዊ መንገድም እንዲሁ ምርት መሰብሰቢያ ማሽን ኮምባይነር በመጠቀም ምርቱ እየተሰበሰበ መሆኑን ገልጸዋል። ለዚህም ክልሉ 29 የኮምባይነር ማሽኖችን አሠማርቶ ከፍተኛ ሥራ እየሠራ መሆኑን ነው ያስረዱት።

እነዚህ ዘመናዊ የምርት መሰብሰቢያ ማሽኖች በተለይም በምሥራቅ ጎጃም፣ በምዕራብ ጎጃምና በሰሜን ሸዋ አካባቢዎች ላይ ሰፊ ሥራ እየሠሩ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አምሳሉ፤ በክልሉ በሰባት ሺ ሁለት መቶ ሄክታር ያህል መሬት ላይ የሚገኝ ምርት በኮምባይነር መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ክልሉ በምርት ዘመኑ ያመረተውን ምርት ለመሰብሰብ ባቀደው ልክ ሰብስቦ አላጠናቀቀም፤ ሌላው ደግሞ በምርቱ የዕድገት መጠን ልክ በቀጣይ ይሰበሰባል። በቀጣይ እስከ ጥር መጨረሻና የካቲት መጀመሪያ ድረስ የሚሰበሰብ ምርት ይኖራል። ጥራጥሬን ጨምሮ የተለያዩ ሰብሎች በዚሁ ወቅት ነው የሚሰበሰቡት።

አሁን አርሶ አደሩ ያለውን አቅም በሙሉ አስተባብሮ በምርት ስብሰባ ላይ እየሠራ ነው ያሉት ኃላፊው፣ ለዚህም ዋናው ምክንያት የእርሻ ሥራውን ካቋረጠ በእጅጉ እንደሚጎዳ ማወቁ ነው ብለዋል። ስለሆነም የክልሉ ግብርና ቢሮ አርሶ አደሩ አቅሙን አሟጦ አቅም በፈቀደለት ልክ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል። አርሶ አደሩ አሁን በክልሉ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ውስጥም ሆኖ የግብርና ሥራውን መሥራቱን አጠናክሮ ቀጥሏል ብለዋል፡፡

አቶ አምሳሉ እንዳብራሩት፤ አርሶ አደሩን በማቀናጀትና በማስተባበር እንዲሁም ቴክኖሎጂን በመጠቀም ረገድ የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ክልሉ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል፤ ለዚህም ቢሮው በርካታ ስልቶችን በመጠቀም ድጋፍ እያደረገ ነው። በየአካባቢው ያሉት የግብርና ባለሙያዎች በክልሉ ችግር በሌለባቸው አካባቢዎች በአካል አርሶ አደሩ ዘንድ በመድረስ አርሶ አደሩን እየደገፉ ናቸው።

በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት የተለያዩ የግብርና መረጃዎች ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ እየተደረገም ነው። ግብርና ዓመቱን ሙሉ የሚሠራ ሥራ እንደመሆኑ ከግብርና ዘመን አቆጣጠር ጋር በማገናኘት በሰብል ስብሰባ፣ በመስኖ ሥራ፣ ችግኞችን በመንከባከብና በመከታተል እንዳይጎዱ፣ እንዳይነቀሉና እንዲጸድቁ የማድረግ መሰል ሥራዎችን አስመልክቶ ተገቢውን መረጃ ለአርሶ አደሩ በወቅቱ ተደራሽ እየተደረገ ነው።

የግብርና ሥራውን ሊደግፉና ሊያሻሽሉ የሚችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም አንጻርም እንዲሁ ከዚህ ቀደም የተለያዩ ድጋፎች ይደረጉ እንደነበር አስታውሰው፤ ይህ ድጋፍ ግን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ዘንድሮ በክልሉ ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት መቀነሱን ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም ከኦሮሚያ ክልል የሚመጡ ኮምባይነሮችን በመጠቀም ከሌሎች አሻጋሪ ከሆኑ ዞኖች ጋር በቅንጅት ይሠራ እንደነበር አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግን እንዲህ አይነቱ የመደጋገፍና የመረዳዳት ሁኔታ መቀነሱን ገልጸዋል።

በክልሉ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብና የግሪሳ ወፍም ተከስቶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ አምሳሉ፤ የመከላከል ሥራውም ተጠናክሮ መሠራቱን ገልጸዋል፡፡ በዚህም ቢሮው ማድረግ የሚገባውን በሙሉ ማድረጉን ተናግረዋል።

‹‹እንደ ግብርና ቢሮ የግብርና ሥራ መቆም የለበትም በማለት የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት እየተሠራ ነው። የትኛውም ነገር ይፈጠር ግብርና ማለት የቀይ መስቀል ሥራ ነው። ቀይ መስቀል ሊሞት ያለና አደጋ የደረሰበት ሰው እንደሚያድን ሁሉ ግብርናም ምግብ አምራች እንደመሆኑ ሥራው አይቆምም፤ መቀጠል አለበት›› በሚል እምነት እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አቶ አምሳሉ እንደተናገሩት፤ ከሜካናይዜሽን አኳያ አርሶ አደሩ የሚፈልገው ምን እንደሆነ በመለየት፤ የተለያዩ ማሽኖች የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሠረት በማድረግ እንዲቀርቡ ይደረጋል። ከኦሮሚያ፣ ከደቡብም፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝም የሚመጣ ከሆነና አስቻይ ሁኔታዎች ካሉ እንዲመጣ ይደረጋል።

ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብና በግሪሳ ወፍ ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠን አስመልክቶም ከወረርሽኙ በኋላ ራሱን የቻለ የባለሙያ ቡድን ተዋቅሮ መረጃ እየተሰበሰበ መሆኑን አቶ አምሳሉ ጠቁመዋል። የግሪሳ ወፍም ሆነ የአንበጣ ወረርሽኝ ስላደረሰው የጉዳት መጠን አሁን መናገር እንደማይቻል አስታውቀዋል።

እንደዚህ አይነት ክስተቶችን ለመቀነስ የግብርና ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት የአደጋ ጊዜ ኮሙኒኬሽን እቅድ አለው ያሉት አቶ አምሳሉ፤ ለምሳሌ አንበጣ፣ ጎርፍ፣ ድርቅ ተምች ቢከሰት ተብሎ የሚዘጋጅ ራሱን የቻለ እቅድ እንዳለም አስታውቀዋል። በዚህም ላይ የሕዝብ ግንኙነቱ ተከታታይነት ያለው እና ኅብረተሰቡ እንዳይወዛገብ ማድረግ የሚችል መረጃ ይሰጣል ብለዋል፡፡

ከሰብል ብክነት ጋር በተያያዘም አርሶ አደሩ በጭቃ ተሰቃይቶ ብርድ፣ ዝናብ ቁርና ፀሐይ ተፈራርቆበት ካመረተው ምርት አብላጫው ይባክናል ያሉት አቶ አምሳሉ፤ አርሶ አደሩ በብዙ ልፋትና ድካም ካመረተው ምርት ከ33 በመቶ በላዩ እንደሚባክን ጥናቶችን ዋቢ አድርገው ገልጸዋል። በተለይም የብርእ ሰብል ቅንጣት ይቆረጣል፤ ከመሬት ንቃቃት ይገባል፤ በከብቶች ሲወቃም እንዲሁ በብዛት ይባክናል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በውቂያ ወቅትም በበሮች ሽንትና እበት ይበላሻል እንዲሁም ከቦታ ቦታ ሲጓጓዝም እንዲሁ ይባክናል። ስለዚህ ይህንን ብክነት ለመቀነስ ሁሉም ሰው መረባረብ ይኖርበታል። ሰብሉን በጥንቃቄ፣ ከብክነት በፀዳ መልኩ መሰብሰብና ለገበያ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

በብዙ ድካምና ልፋት የተገኘን ምርትና ሀብት በአግባቡና በትክክል መጠቀም ካልተቻለ አርሶ አደሩም ሆነ ከተሜው ተጠቃሚ አይሆንም ያሉት አቶ አምሳሉ፤ ማኅበረሰቡ ብዙ ወጪ የሚጠይቁ እንደ ድግስ ያሉትን መቀነስ እንደሚገባም ተናግረዋል። ስለዚህ ስለምርት ብክነት መከላከል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አርሶ አደሩ እንዲገነዘብ ሚዲያው ማስረዳትና ማስገንዘብ እንዳለበትም አስታውቀዋል።

አማራ ክልል በጣም ትልልቅ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች እንዳሉ ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩ እነዚህን የከርሰምድርና የገጸ ምድር ውሃዎች በመጠቀም ሊያጣ የሚችለውን ምርት መተካት ከዚያ በላይም ማምረት እንዳለበት አስታውቀዋል። ይህን አስፈላጊ፣ ወሳኝና የማይቆም የግብርና ሥራን በትብብርና በቅንጅት መሥራት ተገቢና የግድ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

## የተቋማቱ መውጣትና መግባት

ግርማ መንግሥቴ

በሀገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ የለውጡ አየር ከነፈሰባቸው ተቋማት መካከል ትምህርትና የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣንን የመሰሉት ይገኙበታል። የክልል ትምህርት ቢሮዎችና በሥራቸው የሚገኙትንም ለውጡ ዳሷቸዋል። ከእነዚህ የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ተቋማት መካከል የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ፣ የከተማ አስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላትና የመሳሰሉት ናቸው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣንና የከተማው ትምህርት ቢሮ በጋራ በመሆን በ2015 ዓ.ም የሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ ከግል ትምህርት ቤት ተቋማት ጋር ውይይት ማድረጋቸው ይታወሳል። ዓቢይ የመወያያ አጀንዳቸውም አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በሚጠበቀው የጥራት ደረጃ መተግበር የሚገባው ስለ መሆኑ፤ የሥርዓተ ትምህርት ትግበራው ለዜጎች ሁለንተናዊ እድገት የሚያስፈልጉ የትምህርት ጥራትን መሠረት በማድረግ በተለያዩ የትምህርት አደረጃጀት የሚሠጥ መሆኑ እና ከ2015 በፊት በነበረው የትምህርት ዘመን በመርሐ ግብሩ ትግበራ የተገኙ መልካም ውጤቶች እንዳሉ ሁሉ በትግበራ ሂደት የነበሩ ክፍተቶች በቀጣይ መስተካከል ያለባቸው መሆናቸውና የመሳሰሉት ነበሩ።

በወቅቱ በትግበራ ሂደቱ በአንደኛው ምዕራፍ አንደኛ ደረጃ በመካከለኛ ደረጃ የሙከራ ትግበራ በ2014 ዓ.ም የተከናወነበት እና በ2015 ዓ.ም ወደ ሙሉ ትግበራ የሚገባበት ሲሆን፣ በቅድመ አንደኛ እና በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ፤ እንዲሁም በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ላይ የሙከራ ትግበራ የሚደረግ እና በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ወደ ሙሉ ትግበራ የሚገባበት እንደሚሆን መገለፁም ይታወቃል። የአሁኑ ጠንከር ያለ አካሄድም ይህንኑ መነሻ ያደረገ ይመስላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን በደንብ ቁጥር 74/2014 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያስፋፋል፤ ደረጃ ያሳድጋል። እንዲሁም ከደረጃ በታች የሆኑ ተቋማትን እውቅና ፈቃድ የማገድና የመሰረዝ ሥልጣን አለው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን በመዲናዋ የሚገኙ 25 የግል ኮሌጆችና ካምፓሶች ከአንድ ተቋም በስተቀር ሌሎቹ እገዳው እንደተነሳላቸውና በ2016 ዓ.ም የአዲስ ሠልጣኞች ምዝገባ እንዳያካሒዱ ጊዜያዊ እግድ ስለመጣሉ በባለሥልጣኑ የቴሌግራም ገፅ ላይ ዜና ሆኖ ሰፍሯል።

ምንም እንኳን የተለቀቀው ዜና ድፍን ያለና ኮሌጆቹ ባለሥልጣኑ የሚጠይቀውን የምዘና ግብ ሳያሟሉና የምዝገባ ፍቃድ ሳያገኙ ለ2016 ዓ.ም ምንም አይነት አዲስ ሠልጣኝ መቀበል የማይችሉ መሆናቸውን፣ የትምህርት ተቋማቱ አስፈላጊውን የሠልጣኞች መረጃ እስከ ኅዳር 30/2016 ዓ.ም እንዲያቀርቡ መወሰኑን፣ ካላቀረቡ የእውቅና ፍቃዳቸው የሚሰረዝ መሆኑን ወዘተ የሚገልፅ ቢሆንም ጉዳዩን ለማጣራት አዲስ ዘመን አራት ኪሎ ወደሚገኘው ወደ ባለሥልጣኑ ቢሮ ያቀና ቢሆንም የሚመለከታቸውን አካል ለማነጋገር ያደረገው ሙከራ አልተሳካም።

በእገዳ ደብዳቤው ላይ እንደ ተገለፀው እገዳው ባለሥልጣኑ ባወጣው እውቅና ፍቃድ መመሪያ 02/2012 ዓ/ም፣ አንቀፅ 13፣ ንዑስ አንቀፅ 2፤ እንዲሁም አንቀፅ 15፣ ንዑስ አንቀፅ 2 (ዝቅ ብሎ "መመሪያ 01/2014" የሚልም ተጠቅሷል) መሠረት መሆኑ ተጠቅሷል።

በዓለም አቀፍ እና በሀገር አቀፍ ያለውን ተሞክሮ በመቀመር የኢንስፔክሽን ቼክሊስት በማዘጋጀት እና ግንዛቤ በመስጠት በ2014 ዓ.ም ወደ ምዘና መግባቱ የሚያስታውሰው ባለሥልጣኑ የኤንስፔክሽን ሥራው ከተከናወነ በኋላ የተቀመጠላቸው እስታንዳርድ እና ተቋማቱ ያሉበት አሁናዊ ሁኔታ መራራቁን መገንዘቡን በወቅቱ መግለፁ ይታወቃል።

በእነዚህ ማሠልጠኛ ተቋማት የሚያልፉ ሠልጣኞች ብቁ የሆነ፣ ጥራቱን የጠበቀ ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ጥራቱን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን የወሰደው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን ለምሳሌ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በዲአፖል ሆቴል የተደረጉ ተከታታይ ውይይቶች፣ አንደኛውም ሰሞኑን በዚሁ ተቋም የተወሰደው የማስተካከያ ርምጃ ነው።

የማሠልጠኛ ተቋማቱ ወደ እስታንዳርዱ በተቋሙ ቼክሊስትና እስታንዳርድ ኤንስፔክሽን መሠረት እንዲመጡ ለማስቻል ጥረት ሳደርግ ቆይቻለሁ የሚለው ይህ ተቋም፣ ተቋማቱ በቂ ግንዛቤ በመውሰድ ጥራት ያለው ሥልጠና በመስጠት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባቸው በተደጋጋሚ ከመግለፅም ባለፈ ተግባሩ የእለት ተእለት ሥራው እንደሆነም በኃላፊዎቹ አማካኝነት ሲነገር ቆይቷል።

ባሳለፍነው ሳምንት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት፣ በባለሥልጣኑ የትምህርት ሥልጠና ጥራት ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደረጀ ሙሉጌታ እንደሚሉት ባለሥልጣኑ በደንብ ቁጥር 74/2014 የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን የሚያመላክት ነው። በሀገራችን አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ እየተደረገ ቢሆንም አንዳንድ ተቋማት ሥርዓተ ትምህርቱን በመጣስ የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያከናውኑ መሆኑን በኢንስፔክሽን ግኝት በመታወቁ ይህንን አሠራር በማስተካከል ሁሉም ተቋም በሀገሪቱ ባለው ሥርዓተ ትምህርት በአግባቡ መተግበር ይኖርባቸዋል።

ተቋማት ላይ ጥራትን የማረጋገጥ ሥራ በየግዜው የሚሠራ ሲሆን፣ አጠቃላይ የሚሰጡት ትምህርት ተገቢነቱን፣ በተለይም ሥርዓተ ትምህርቱን ጠብቆ መሄዱን እንደ አዲስ አበባ ከተማ ስታንዳርድ ኢንስፔክሽን ብቻ ሳይሆን፤ በተጨማሪ፣ በድንገተኛ የኢንስፔክሽን ትግበራ በስፋት ይከናወናል።

ከዚህ አኳያ የትምህርት ቤትና በየደረጃው ያሉት አስፈፃሚ ተቋማት አመራሮች ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ክፍተቶችን የመለየት ሥራ ይሠራል። ተቋማቱ እንዲያሻሽሉ ይደረጋል፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ ተቋማትን ተጠያቂ የማድረግ ሥራ ይከናወናል። በተጨማሩም ተቋማት ሥርዓተ ትምህርቱን ጠብቀው አጠቃላይ የማስፈጸም መመሪያዎችንና ፖሊሲዎችን መነሻ በማድርግ የተጣጣመ መሆኑ የሚረጋገጥበት አግባብ መኖሩን የገለጹ ሲሆን፣ የጥራት ቁጥጥርና ክትትል ሥራ ተጠናክሮ ይሠራል።

ሐምሌ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ከደረጃ በታች በሆኑ 12 ትምህርት ቤቶች ላይ እርምጃ መውሰዱን፤ የተማሪዎችን ውጤት የሚገልጽ መረጃ ለተማሪዎችና እውቅና ፍቃድ ለሰጣቸው አካል እንዲያስረክቡ ማስታወቁን በወቅቱ ይፋ አድርጎ የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ዘንድሮም በተመሳሳይ አካሄድ ላይ መሆኑን የሚያሳዩ አሠራሮች ቢኖሩትም፣ የመታገድና አለመታገድ ምክንያትና መስፈርቶቹ ምን ምን እንደሆኑ የትምህርት ባለ ድርሻ አካል ለሆነው ኅብረተሰብ በአብዛኛው ግልፅ ባለመሆኑ ያለማሰለስ መረጃዎችን ተደራሽ ቢያደርግ የተሻለ ሥራን እንደሚሠራ በብዙዎች የሚሰጥ አስተያየት ነው።

> ‹‹ባለሥልጣኑ የተቋማቱን የትምህርት መስኮች የፈቃድ ጊዜ ያለበትን ደረጃ ለማሳየት በየትምህርት መስኩ፣ በካምፓስ እና በፈቃድ ጊዜው ላይ በአረንጓዴ፣ በቢጫ፣ በቀይ እና በወይን ጠጅ ቀለማት ምልክት ያደረገ ሲሆን፤ አረንጓዴ የተደረገባቸው "የፈቃድ ጊዜያቸው ከ6 ወራት በላይ የሚቆይ እና አዲስ ተማሪ መመዝገብ የሚችሉ" ፤ ቢጫ የተደረገባቸው "የፈቃድ ጊዜያቸው ከ1 እስከ 6 ወር በላይ የሚቆይና አዲስ ተማሪ መመዝገብ የሚችሉ ናቸው ››

ሰሞኑን በኢፌዴሪ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ካሰራጨው መረጃ መረዳት እንደ ተቻለው በአጠቃላይ የ382 ተቋማት ወቅታዊ የፈቃድ መረጃ ይፋ የተደረገ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል 366 የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (5 የግል ዩኒቨርሲቲዎች፣ 6 የግል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች፣ 6 ኢንስቲትዩቶች እና 349 የግል ኮሌጆች) ሲሆኑ፤ 16ቱ ደግሞ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (4 የርቀት ትምህርት ፈቃድ የወሰዱ፤ እንዲሁም፣ 12 የመደበኛ ትምህርት ፈቃድ የወሰዱ) ናቸው።

ባለሥልጣኑ የተቋማቱን የትምህርት መስኮች የፈቃድ ጊዜ ያለበትን ደረጃ ለማሳየት በየትምህርት መስኩ፣ በካምፓስ እና በፈቃድ ጊዜው ላይ በአረንጓዴ፣ በቢጫ፣ በቀይ እና በወይን ጠጅ ቀለማት ምልክት ያደረገ ሲሆን፤ አረንጓዴ የተደረገባቸው "የፈቃድ ጊዜያቸው ከ6 ወራት በላይ የሚቆይ እና አዲስ ተማሪ መመዝገብ የሚችሉ፤ ቢጫ የተደረገባቸው "የፈቃድ ጊዜያቸው ከ1 እስከ 6 ወር በላይ የሚቆይና አዲስ ተማሪ መመዝገብ የሚችሉ" ናቸው።

ነገር ግን በቀሩት 6 ወራት ፈቃድ ሳያሳድሱ አዲስ ተማሪ መመዝገብ የማይችሉ፤ ቀይ ቀለም የተደረገባቸው "ፈቃድ ያላሳደሱና የፈቃድ ጊዜያቸው ያለፈ በመሆኑ ምክንያት አዲስ ተማሪ መመዝገብ የማይችሉ መሆናቸውን፤ እንዲሁም፣ ወይን ጠጅ ቀለም የተደረገባቸው" ያቋረጡ ስለሆነ አዲስ ተማሪ መመዝገብ የማይችሉ፤ የተመዘገቡ ተማሪዎችን ግን ማስጨረስ ያለባቸው መሆናቸውንም በዝርዝር አስፍሯል። ኅብረተሰቡ በየተቋማቱ ከመመዝገቡና ማስመዝገቡ በፊትም እነዚህን ባለ ቀለም ምልክቶች በአግባቡ ማጤን እንዳለበት ባለሥልጣኑ አሳስቧል።

የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን፣ ለአጠቃላይ መረጃ ሲባል፣ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፈቃድ ያገኙበትን የትምህርት መስክ፣ ካምፓስ እና መርሐ ግብር አሟልቶ የያዘና በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፈቃድን የማግኛ ድረ-ገጽ በመክፈት ሊንኩን (https://bit.ly/43Z1Rck) ለሕዝብ ይፋ አድርጓል።

የትምህርት ተቋማት ለደረጃው በተቀመጠው መስፈርት መሠረት አሟልተው ባለ መገኘታቸውና ከደረጃ በታች በመሆናቸው የተማሪዎች ውጤት፣ ብቃትና ክሂሎት እያሽቆለቆለ ለመምጣቱ ለምሳሌ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ነው። ይህ እየተነገረ ባለበት በዚህ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣንም ሆነ እንደ አገር በኢፌዴሪ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እየወሰዱት ያለው ርምጃ ችግሩን ከመሠረቱ ይፈታዋል የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ አለ።

ስለዚህ ተቋማቱ ይህንን የባለ ድርሻ አካላትን አደራና እምነት ከግምት በማስገባት የበለጠ እንደሚንቀሳቀሱ እምነት እንደሚኖር ይጠበቃል። ኅብረተሰቡም እንደ አንድ የትምህርት ባለድርሻ አካል በትምህርት ጉዳይ ላይ ችግሮችን ከተመለከተ በነፃ የስልክ መስመር 9302 ‹‹ሃሎ›› ብሎ ችግሩን ማሳወቅ ይችላል። ይህን ከሆነ "ባለ ድርሻ አካላት›› የሚለው ቃል ኅብረተሰቡን በትክክል የሚገልፅ ይሆናል።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረተው ምርት ጎረቤት ሀገራትን ጭምር እየመገበ ነው ››

*- መለስ መኮንን (ዶ/ር)*
*የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ*

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**ኢትዮጵያ ግብርና የሕልውና መሠረቴ ነው በማለት በሰፊው እየሠራች ትገኛለች። በአሁኑ ወቅት እየታመሰ የሚገኘውን የዓለም ገበያ በተለይም ደግሞ በምግብ ፍጆታ ራስን ማሸነፍ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን በማመን ሀገሪቱ ለግብርና ዘርፍ ትኩረት መሰጠቷ የሚበረታታ ነው።**

**መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም በኢትዮጵያ ሰፊ የሚታረስ መሬት ቢኖርም አሁንም ድረስ የምግብ ዋስትናን በቅጡ ማረጋገጥ አልተቻለም። በመሆኑም መንግሥት ሳለፉት አራት ዓመታት በሰፊው ፊቱን ወደ ግብርና ያዞረ ሲሆን ስንዴን ከውጭ ማስገባት ማቆሙንና የሀገር ውስጥ ፍጆታ መሸፈኑን ተናግሯል።**

**በአሁኑ ወቅትም ግብርናን በማዘመንና በቀጣይ የሀገሪቱን አቅም ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ተግባራት በመከናወን ላይ መሆናቸው ይነገራል። በተለይም የግብርና ሚኒስቴር የ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ በመከተል በርካታ ውጤቶችን ለማስመዝገብ እየታተረ መሆኑ ሲገልጽ ይሰማል። በስንዴ፣ ሩዝ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የቀባት እህሎችና ሌሎች ዘርፎችም ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረጉን ሚኒስቴሩ ይናገራል።**

**በዛሬው ዕትማችን የግብርና ሚኒስቴር አሁናዊ እንቅስቃሴዎችና ቀጣይ ትኩረቶችን አስመልክቶ የዝግጅት ክፍላችን በግብርና ሚኒስቴር የአርሻና ሆርቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ፤ መለስ መኮንን (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጓል፤ መልካም ንባብ።**



**አዲስ ዘመን፡- የግብርና ሚኒስቴር በሁሉም ዘርፍ ምርታማነትን ለማሳደግ እና የገበያ ፍላጎትን ለማሟላት ምን እየሠራ ነው?**

**መለስ (ዶ/ር)፡-** ግብርና ለሀገራችን በጣም ወሳኝ ነው። የግብርና ሚኒስቴርም ዘርፉ ለአገር ያለውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአስር ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቷል። ይህ እንዲሁ የተዘጋጀ ሳይሆን በተለያዩ ወቅቶች የተደረጉ ምክክሮች፣ ወርክሾፖችና አሁናዊ ሁኔታዎችን በማገናዘብም የተዘጋጀ ነው። የ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ሲዘጋጅም የምርምር ተቋማት፣ የሀገራችንን ግብርና የሚደግፉ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶችና ደጋፊ አካላት፣ የመንግሥት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላትም በሙሉ ተሳትፈውበታል።

እነዚህን አካላት በማሳተፍ የተሻለ ስትራቴጂክ እቅድ ማዘጋጀት ተችሏል። ነገር ግን ሀገሪቱ ካላት አቅም አኳያ ብሎም ለግብርና ምቹ ከመሆኑ አንፃር መታረስ የሚችል ሰፊ ምርታማ መሬት አላት። ለዚህም ምቹ የሆኑ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች፣ ተስማሚ የአየር ንብረት ብሎም ለመስኖም ሰፊ ውሃ ያላት ሀገር ናት።

ካለው ተስማሚ የአየር ንብረት የተነሳ በኢትዮጵያ ዓመቱን ሙሉ የግብርና ምርት ማምረት ይቻላል። በእንስሳት ግብርና ላይም በስፋት ተጠቃሚ መሆን ይቻላል። የሕዝብ ቁጥር ትልቅ ሃብት ነው። አንዳንድ ጊዜ የሕዝብ ሃብት እንደ ችግር ይታያል። ነገር ግን እንደ እኛ ሀገር ያለው ሕዝብ በአግባቡ ከተያዘ፤ አምራች እንዲሆን ከተሠራ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው።

65 ከመቶ የሕዝባችን ቁጥር አምራች ወይንም መሥራት የሚችል ነው። ይህ ካስተባበርነው ተዓምር የሚሠራ ኃይል ነው። እኛ ያለን ይህ ሃብት በርካታ ሀገራት የሌላቸው ሃብት ነው። በእርግጥ ይህ ሁሉ ሃብት እያለን ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ መጠቀም የሚገባትን እየተጠቀመች አልነበረም፤ አሁንም እየተጠቀመች አይደለም። በመሆኑም በ10 ዓመቱ እቅድ ውስጥ የመጣንበት የዘመናት አካሄድ አዋጭ ስላልሆነ ለየት ያለ አካሄድ መንደፍ ግድ ብሎናል። አሁን ባለን እቅድ ጊዜ የለንም በሚል መንፈስ እየሠራን ነው። በተለይም በአስር ዓመቱ እቅድ በጣም ልንረባረብ ይገባል ብለን 10 ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገናል።

ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው የስንዴ ምርታማነትን ማሳደግ ሲሆን ይህን በበጋ እና በመስኖ እርሻ በሰፊው መሠራት አለበት ብለን በትኩረት እየሠራንበት ነው። ሀገራችን ለስንዴ ምርት በጣም ምቹ ናት። በሦስት ዙር ማለትም በመኸር፣ መስኖ እና በልግ ስንዴ ማምረት የሚቻልባት ሀገር ናት። ነገር ግን በመስኖ እና በልግ አናመርትም ነበር። ምርታማናትንም ይጨምራል ብለን አናስብም ነበር። አሁን ሦስቱም ላይ ትኩረት አድርገን ውጤታማ እያደረግን ነው።

በየዓመቱ ሀገራችን ስንዴ ለመግዛት እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ታወጣለች። ይህም ብቻ ሳይሆን ሀገራችን ይህን ሁሉ የማምረት አቅም እያላት ስንዴ እየተሰፈረላት ወይንም ስንዴ የምትመፀወት ሀገር መሆን ስለሌለባት ይህን ለማስቀረት ደግሞ ጠንክር ብሎ መሥራት ይገባል በሚል እሳቤ የተጀመረ ነው።

የሀገር ውስጥ ስንዴ ፍላጎት ማሟላት በሚለው ዓላማ ላለፉት አራት ዓመታት ስንሠራ በመቆየታችን በየዓመቱ ካሰብነው እና ካቀድነው በላይ እቅዳችንን እያሳካን ነው። በመንግሥት ተቋማት፣ የምርምር ማዕከላት እና ባለሙያዎች በመተባበር እና ከላይ እስከ ታች ያሉ አመራሮች በመናበብ ትልቅ ለውጥ ተመዝግቧል። ስንዴ አምራች ያልነበሩ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት ትልቅ ምርት የሚገኝበት አካባቢም ሆነዋል። ለአብነትም በኦሮሚያ ክልል በስንዴ የሚታወቁት ባሌ እና አርሲ ነበሩ። ጅማ እና መካከለኛ ሸዋ ላይ ብንመጣ ብዙም ስንዴ ምርት አይታወቅም ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን በስንዴ ምርት ወደፊት መጥተዋል። በደቡብ፣ አፋር እና ሶማሌ፣ አማራ ክልልም በሰፊው እየተሠራ ነው።

አሁን ደግሞ ትግራይን ክልል ጨምረን ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በዚህ ዓመትም በመኸር መሥራት ያለብንን ሥራ እየሠራን ነው። በበጋው ደግሞ በመስኖ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ በመሸፈን ወደ 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው። እስካሁን ድረስ ቀድመው ምርት በሰበሰቡና ቀድሞ ዘር መዝራት ባለበት አካባቢ እየተረባረብን ስንዴ እየዘራን ነው። በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ በዘር ተሸፍኗል። ሌሎች አካባቢዎችም ምርት እያነሱ የሚሄዱ በመሆኑ በእርግጠኝነት ይህን ሦስት ሚሊዮን ሄክታር በስንዴ እንሸፍናለን።

ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ለማስቀረት እና ውጤታማ ለመሆን መሥራት አለብን በሚል የጀመርነው በጣም የተሳካ ነው ብለን እናስባለን። ይሁንና ይህ ሁሉ ምርት እየተመረተ ተጠቃሚው ጋር እንዴት እየደረሰ ነው የሚለውን ማየት ይገባል። ስንዴ ብቻ ሳይሆን አኩሪ አተር እና ሩዝ ላይ በልዩ ትኩረት ላይ እየሠራን ነው። ይህ ብቻ አይደለም በመኸርም በሠራነው ሥራ እና የቆዩ ዓመታትን ዳታ ብንመለከትም የምርት መጠን እየጨመረ ነው። ነገር ግን ገበያ ላይ ስንሄድ ዋጋው ይጨምራል ወይንም ደግሞ የምርት እጥረት ይኖራል። ይህን ለምን ሆነ የሚለውን በደንብ ማየት ይገባል። የተመረተው ምርት የት እየገባ ነው ብሎ መረዳት ይፈልጋል። ምርት እየተመረተ አይደለም እንዳይባል በከፍተኛ ሁኔታ ምርታማናት እየጨመረ ነው። በዘመናዊ ማሽኖች ጭምር እየተመረተ ነው። ስለዚህ ምርቱ የት እየገባ ነው? የሚለው ማጤን ይገባል።

ለዚህ አንደኛው ችግራችን የገበያ ሰንሠለቱ ደካማ መሆን ነው። በዚህ ላይ በደንብ መሥራት አለብን። ይህን በተመለከተ ሌሎች ሚኒስትሮች እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር እየሠራን ነው፤ መፍትሔም ይኖረዋል።

ሌላው በመኸር፣ መስኖ እና በልግ የምናመር ታቸው ምርቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ እየቀለበ ነው ብዬ አላምንም፤ ይህ የእኔ እምነት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረተው ምርት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን የጎረቤት ሀገራትን ሕዝብ ጭምር እየመገበ ነው ማለት ስህተት አይሆንም። ጅቡቲ እና ሶማሊያ በርካታ ግብርና ምርቶችን ከኢትዮጵያ ይሄድላቸዋል። ሰሜን ኬኒያ እና ሶማሌ ላንድም ከኢትዮጵያ በርከት ያሉ ምርት ይሄድላቸዋል። በተመሳሳይም ሱዳን እና ኤርትራም ከኢትዮጵያ ምርቶችን ይወስዳሉ። 360 ዲግሪ ዙሪያውን ብንመለከት ከኢትዮጵያ ምርት ይወስዳሉ። ጎረቤት ሀገራት ከኢትዮጵያ ምርት መውሰዳቸው ክፋት የለውም፤ ኢትዮጵያም ከእነዚህ ሀገራት የተለያዩ ምርቶችን ልትወስድ ትችላለች። ትልቁ ቁም ነገር እነዚህ ከሀገር ውጭ የሚሄዱ ምርቶች በደንብ ‹‹ሬጉሌት›› ተደርገው ለሀገር ጥቅም በሚያስገኝ እና የውጭ ምንዛሪ በሚያመጣ መልኩ ቢሆን በጣም ጥሩ ነው። ይሁንና አብዛኛው ሕገወጥ በሆነ መንገድ ነው የሚወጣው። ስለዚህ በግብርና ላይ ያለን አመራሮች እና ባለሙያዎችም ጊዜ የለንም በሚል መንፈስ ምርታማናትን ለመጨመር መሥራት አለብን።

ሌላው በግብይት እና ቁጥጥር ሴክተር ላይ በጋራ መሥራት አለብን። በንግዱ ማኅበረሰብ ላይ ያሉትም ሀገርን በሚጠቅም መንገድ መሥራትና የዋጋ ንረትን በሚቀንስ መንገድ በኃላፊነት መሥራት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የግብርና ምርት መጨመር እንደተጠበቀ ሆኖ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትና ምርታማነት አለመመጣጠን ችግር ፈጥሯል የሚል የሰላ ትችትም አለ። እርስዎ ምን ይላሉ?**

**መለስ (ዶ/ር)፡-** የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር ፍጆታ ይጨምራል፤ ይህ ለጥያቄ እና ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። ነገር ግን የሕዝብ ቁጥር በጣም እየጨመረ ቢሆንም ምርትና ምርታማነትም በዚያው ልክ እየጨመረ ነው። ከሕዝብ ቁጥራችን መጨመር ይልቅ በሕገ ወጥ መንገድ የሚወጣው ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳን ነው። ለምሳሌ ስንዴ ከውጭ ማስገባት አቁመናል። አሁን ገበያ ላይ የስንዴ እጥረት የለም። ዳቦ ቤቶችም የስንዴ ዱቄት አለ። ግን ምርት በመያዝ ዋጋ የመጨመር አዝማሚያ አለ። በእርግጥ በቂ ሥራ ሠርተናል ብለን ማሰብ የለብንም፤ ገና ብዙ ሥራ መሥራት አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- በአስር ዓመቱ እቅድ ውስጥ አንዱና ትልቁ የቀባት እህሎች ላይ ያለውን ምርታማነት እና አቅም ማሳደግ ነው። ሚኒስቴሩ በዚህ ላይ ራሱን እንዴት ይገመግማል?**

**መለስ (ዶ/ር)፡-** ከስንዴ ቀጥሎ ሁለተኛው ፕሮግራማችን የቅባት እህሎች ላይ ሲሆን፤ ዘይትን በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚገባውን ምርት

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረተው...

ከ ገጽ 9 የዞረ

መተካት ነው። በዚህ ላይ የሚሠሩ በርካታ ተቋማት አሉ። ንግድ ሚኒስቴርና እና ሌሎች ሚኒስትሮችም አሉ። በርካታ ፋብሪካዎችም እየተተከሉ ነው። ለእነዚህ ፋብሪካዎች ደግሞ ግብዓት ማቅረብ ተገቢ ነው። ለውዝ እና ሌሎች ቅባት እህሎችን እያመረትን ነው። በልዩ ትኩረት አኩሪ አተር ላይ እየሠራን ነው፤ በሰፊው ተመርቷል። ነገር ግን ላመረትነው አኩሪ አተር ምርት ገበያ እያጣን ነው። አርሶ አደሩ ያመረተውን አኩሪ አተር የሚገዛው የማጣት እና ዋጋ መቀነስ ይታያል። ይህ ደግሞ በኤክስቴንሽን ሥርዓታችን አኩሪ አተር ምርትን ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ላይ የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በዚህ ላይ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብሎም ከሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን የገበያ ችግሩን ለማቃለል፣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የምንሠራው ይሆናል።

ከሩዝ ጋርም በተያያዘ በሰፊው እየተሠራ ነው። ለተወሰኑ ዓመታት በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ሩዝ ይመረት ነበር። አማራ ክልል ፎገራ አካባቢ ሰፋ ባለ መልኩ ይመረት ነበር። ብዙውን ጊዜም ሩዝ ለምግብነት የምናውልበት ልምድ አናሳ ስለሆነና የአንድ አካባቢ ምርት አድርጎ ማሰብም ስለነበር ከአማራ ክልል ውጭ ብዙም የተስፋፋ አልነበረም። ላለፉት ሦስት ዓመታት በርካታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንገኛለን። ካለፈው ዓመት ጀምሮ በኦሮሚያ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማስፋፋት ሥራ ሠርተናል፤ አልፍ ሲልም በሱማሌ ክልል የማስፋፋት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። በየዓመቱ እስከ 300ሺ ሄክታር ሩዝ ነበር የሚሸፈነው። በዚህ ዓመት ግን አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሩዝ ተሸፍኗል።

ከአማራ ክልል በመቀጠል በኦሮሚያ ክልል በሩዝ ሰፊ ክላስተር ተሸፍኗል። በስንዴ እና አኩሪ አተር ልክ ሩዝ ላይም እየሠራን ነው። ሩዝ ስናመርት በየዓመቱ ከውጭ የሚመጣው ምርት ለመተካት ነው። በአሁኑ ወቅት የሩዝ ምርት ፍጆታም እየጨመረ ነው። በተለይም አፋር እና ሶማሌ ክልል ከፍተኛ ፍጆታ አለ። ስለዚህ ትልቁ ዓላማችን ከውጭ የሚገባው ሩዝ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ነው።

በአትክልትና ፍራፍሬ ላይም ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው። በተለይም ሽንኩርት እና ቲማቲም ላይ አፅንዖት ሰጥተናል። ፍራፍሬ በተመለከተም አቮካዶ፣ ሙዝ እና ማንጎ ላይ በሰፊው እየሠራን ነው። አቮካዶ በደቡብ፣ ሲዳማ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ አማራ እና ኦሮሚያ ክልል እየተሠራ ነው። በተለይም የተሻሻሉ ዝርያዎችን በመምረጥ በየዓመቱ ተከላ እያደረግን እና ወደ ውጭ የሚላከውን ምርት በመጨመር እየላክን ነው። በሀገር ውስጥም ምርትን በማቀነባበር የአቮካዶ ዘይት በማምረት ለውጭ ገበያ የሚውል ምርት እየተመረተ ነው። ማንጎ ላይም ትልቅ አቅም አለ። ነገር ግን ችግር እየገጠመን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ምንድን ነው የገጠማችሁ ችግር ?**

**መስስ (ዶ/ር)፡-** ከማንጎ ጋር ተያይዞ ያለው ማንጎ በተለይ በሲዳማ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ኢትዮጵያ ላይ ትልቅ አቅም አለ። በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎችም በተመሳሳይ መልኩ አቅሙ ትልቅ ነው። ድሬዳዋ እና ሐረር አካባቢም ትልቅ ምርት ይመረታል። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተቸገርን ያለነው በማንጎ በሽታ ነው። ምርትን ከጥቅም ውጭ እያደረገ ሲሆን፤ አርሶ አደሮችንም እንደመፍትሔ እየወሰዱ ያሉት ቀደም ብለው የተከሉትን ትልልቅ ማንጎ ዛፍ በመንቀል አዳዲስ የተሻሻሉ ተክሎችን ወይንም ማንጎ ችግኞችን መትከል ነው።

ይህ ማለት ግን ከባድ ነው። ማንጎ ምርት ለመስጠት ረጅም ዓመታት የሚወስድ ሲሆን፤ ምርት እየሰጠ የሚቆየውም ረጅም ዓመታትን ነው። ስለዚህ አርሶ አደሮቻችን በዚህ ጉዳይ መፈተን



የለባቸውም። በመሆኑም ችግሩን ለማቃለል በርካታ ምርምሮች እየተደረጉ ነው። የምሑራንን ምክረ ሃሳቦችን ይዘን ሥራ እየሠራን ነው። በተለይም ደግሞ ሥነ ሕይወታዊ የመከላከያ ዘዴ መጠቀም አንዱ ሲሆን፤ ይህ ወደ ተግባር ሲገባም አዋጭም ነው። በርካታ መፍትሔዎችን አንድ ላይ አካተን የምንሠራበት አሠራር መኖር አለበት። አይሲፔኤ (icipe- International Centre of Insect Physiology and Ecology) የሚባለው ድርጅትም በዚህ ላይ እየሠራ ነው። በዚህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ኬኒያ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ታንዛኒያን ጨምሮ በአራቱ ሀገራት ላይ የሚሠራ ፕሮጀክት ነው። በዚህ ፕሮጀክት ላይ የሚገኝ ውጤትን በሌሎች ፕሮጀክቶች እና የኢትዮጵያ ክፍሎች የማስፋፋት ሥራም ይከናወናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከማንጎ በሽታ መበራከት አንዱ ያልተመረጡ ዘሮችን በዘፈቀደ መጠቀም እንደሆነ ይነገራል። በዚህ ላይ ሚኒስቴሩ በቂ ትኩረት ሰጥቷል?**

**መስስ (ዶ/ር)፡-** ይህን ለመቋቋም እንደ ሀገር እየሠራን ያለውና በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ሥራ ‹‹በኳንታይን›› ሥርዓታችን ማዘመን ነው። የማንጎ ዘር ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል እናጓጉዛለን። በማንጎ የዘር ምንጭነቱ በትክክል ከታወቀ አካባቢ ብቻ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይገባል። ይህ ሲደረግ የማንጎ በሽታ ከአንዱ ቦታ ሌላ ቦታ እንዳይሄድ ወይንም እንዳይዛመት ያደርጋል።

አጠቃላይ ግን በማንጎም ሆነ በስንዴ ወይንም በግብርና ምርት ላይ ስናወራ እና ምርትና ምርታማነትን እንጨምራለን ስንል በርካታ ፈተናዎች እንዳሉም እንገነዘባለን። ከመነሻው ቴክኖሎጂ ከማግኘት ጀምሮ፣ ዘመናዊ አሠራር፣ ዘመናዊ የግብርና ማኔጅመንት ሥርዓት እና እንክብካቤ በአግባቡ መሥራት፣ ግብዓት አጠቃቀምን እና ሌሎችንም አካቶ በዚህ ላይ መሥራት አለበት። በእርግጥ ከእነዚህ

> **ጅቡቲ እና ሶማሊያ በርካታ ግብርና ምርቶችን ከኢትዮጵያ ይሄድሳቸዋል። ሰሜን ኬኒያ እና ሶማሌ ሳንድም ከኢትዮጵያ በርከት ያሉ ምርት ይሄድሳቸዋል። በተመሳሳይም ሱዳን እና ኤርትራም ከኢትዮጵያ ምርቶችን ይወስዳሉ። 360 ዲግሪ ዙሪያውን ብንመለከት ከኢትዮጵያ ምርት ይወስዳሉ**

ፈተናዎች ሁሉ የሚከፋው በተለያዩ ወቅቶች የሚከሰተው በሽታ ነው። በስንዴ ላይ በተለይ ዋግ እና ‹‹ፋዛሪየም›› በጣም አስቸጋሪ ሲሆን፤ ትልቅ ክትትል የሚጠይቅ ነው።

‹‹ፋዛሪየም››ን ለመከላከል ወቅቱ አጭር ከመሆኑ የተነሳ ይህ ትንሽ ካለፈ ማሳው በሙሉ ከመበከል አያድነውም። ይህን ተከታትሎ ከመከላከል አኳያ ደግሞ ባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ እና ሥልጠናዎችን መስጠት ተገቢ ነው። ባለሙያዎችን ማቀናጀትም ትልቅ ሥራ ነው። ዋግ እና ፋዛሪየም ለመከላከል የሚያስችሉ ኬሚካሎች በየጊዜው አቅርቦት አለ። በመሆኑም የመከላከሉን ሥራ ጎን ለጎን እየሠራን ነው። በአጠቃላይ በሽታ እና ተባይ ላይ ያሉ ሥራዎች ጎን ለጎን በፍጥነት ካልተሠሩ በስተቀር ምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል።

ሌላው ትኩረት የምንሰጠው ቅድመ ማምረት ያለው ሂደት ነው። በተለይ ደግሞ ልዩ ትኩረት መስጠት ያለበት ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ የምንሰጠው ትኩረትና አያያዝ አናሳ መሆን ነው። የሚፈለገውን የምርት መጠንና ጥራት ለማግኘት በዚህ ላይ በሚገባ መሠራት አለበት። ድህረ ምርት ለአዝርዕት ምርት የከፋ ችግር ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን አትክልትና ፍራፍሬ ላይ በጣም ወሳኝ ነው። በዚህ ላይ ያለውን አሠራር ባለሙያው ማሠልጠን፤ ለአርሶ አደር ማሳየትና ቴክኖሎጂ መጠቀም ተገቢ ነው። እስከ ዛሬ የድህረ ምርት ስብሰባ ስትራቴጂ አልነበረንም፤ አሁን ግን ይህንኑ ለማስፈፀምም መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል።

ይህ ሂደት ላይ ነው። በድህረ ምርት ከከረጢት ጀምሮ ምን ዓይነት ጎተራዎችን እንጠቀም የሚል መመሪያም አለ። አትክልትና ፍራፍሬ ላይም ስንሄድ ሳይበላሹ ለረጅም ጊዜ የሚቆይበትና ወደ ገበያ የሚቀርብበት አሠራርና ብልሃት ምንድን ነው? የሚለው ወደ ሥራ እየተገባበት ነው። ይህን ለማዘጋጀት በዘርፉ ላይ ልምድ ያላቸው በርካታ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል። ይህ ሥራ በአዝዕርት፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ በእንስሳትና በተፈጥሮ ሃብት ላይም የሚሠሩ ሥራዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ግብርናን ለማዘመን የኤክስቴንሽን፣ መስኖና መካናይዜሽን ሂደታችን ለማጠናከር ሚኒስቴሩ ምን እየሠራ ነው?**

**መስስ (ዶ/ር)፡-** የአስር ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅዳችን ቴያዥና ተመጋጋቢ ጉዳዮችን የያዘ ነው። በዚህም ኤክስቴንሽን፣ መስኖና መካናይዜሽን በሰፊው የምንሠራበት ጉዳያችን ነው። ቀደም ሲል ዲዛይን የተደረገው የኤክስቴንሽን ሥርዓችን እስካሁን ድረስ ያለው የኤክስቴንሽን ሲስተማችን በጣም የተጠና ነው፤ ይህን ላደረጉትም እውቅና መስጠት ተገቢ ነው። አደረጃጀቱ ለእኛ ሀገር በጣም አስፈላጊ ነው። የእኛ በጣም ሰፊ የሆነ ሥርዓትና የሰው ኃይል የተሠማራበት ነው።

ችግሩ ይህን በአግባቡ መከታተል እና በሙሉ አቅም ማስፈፀም ላይ ክፍተት አለ። ይህን ባለብዙ ተዋናይ አድርገን አዘጋጅተናል። በቀጣይ ይህን ወደ ትግበራ ይገባል ብለን እናስባለን። በዚህ ሴክተር ውስጥ በርካታ ተዋንያን ያስፈልጋሉ። መንግሥት በበላይነት እየመራው የግሉ ሴክተር፣ ዩኒየኖች እና ባለድርሻ አካላትም የሚሳተፉበት ሥርዓት መኖር አለበት። በአጠቃላይ ኤክስቴንሽን፣ መስኖና መካናይዜሽን ላይ በሰፊው እየተሠራበት ነው። ግብርና ሕልውናችን በመሆኑ የአንድ ወቅት ሥራ ሳይሆን በየጊዜው እየሠራን፤ የጎደለንን እያጠናከርን እንሄዳለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበርዎት ቆይታ እና ስለሰጡትን ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**መስስ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## በእድሜ ትንሿ ኢትዮጵያዊት ሞዴል

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የሞዴሊንግ ሙያ የእድሜ ገደብ ያልተቀመጠለት የሙያ ነው። ለሙያ ፍቅር ያለው ማንኛውም ሰው አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን አሟልቶና ተምሮ የሙያው ባለቤት መሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስ በሀገራችን የተለመደውና ወደ ሙያውን ሲገቡ የምናያቸው አብዛኛዎቹ በወጣትነት እድሜ ክልል ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ባልተለመደ መልኩ በእድሜያቸው በጣም ትንሽ የሆኑ ታዳጊዎች ሙያውን ሲቀላቀሉ ይስተዋላል።

ከሰሞኑ የአስራ አንድ ዓመት እድሜ ያላት ታዳጊ ‹‹በእድሜ ትንሿ ኢትዮጵያዊት ሞዴል›› በሚል በአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ ላይ ስሟ መስፈሩ ይታወሳል። የሚገርመው ግን በአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ ላይ የሚሰፍረው የኢትዮጵያውያኑ ስም በዚች ታዳጊ ብቻ የሚያቆም አለመሆኑ ነው። ኢትዮጵያውያኑ የራሳቸውን ሪከርድ በራሳቸው ለመስበር ቆርጠው የተነሱ እስኪመስል ድረስ አንዱን አድንቅን ሳንጨርስ ሌላው አስደናቂ ክስተት ሆኖ ብቅ ይላል። እናም አሁን ላይ ከአስራ አንድ ዓመቷ ታዳጊ በእድሜ በጣም የምታንስ ኢትዮጵያዊት ሞዴል ብቅ ብላለች።

ሞዴል ፍቅር አሸናፊ ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው በአዲስ አበባ ነው። እድሜዋ ስድስት ዓመት ሲሆን የአንደኛ ክፍል ተማሪ ናት። ሞዴል ፍቅር ገና በለጋ እድሜዋ የሞዴሊንግ ፍቅሩ በውስጧ አድሮባታል። ቤት ውስጥ የምታከናወናቸው እያንዳንዳቸው ተግባራት የአለባበስ ምርጫዋ እና አረማመዷ ጭምር ሙያው በውስጧ ነፍስ መዝራቱን በደንብ እንደሚጠቁም ወላጆቿ ይመሰክራሉ።

በተለይ በቴሌቪዥን የምታያቸውን ትርዒቶች ወደ ተግባር በመቀየር ለእናቷ የምታሳይበት መንገድ ሙያው ውስጧ እንደሆነ ከሚያሳዩ ድርጊቶች መካከል አንዱ ነው። ዝንባሌዋን በውል የተገነዘቡት የፍቅር ወላጆች ወደ ሞዴሊንግ ሙያ እንድትገባ የሚያስችላትን መንገድ ጠርገውላታል። በመሆኑም የሞዴሊንግ ትምህርት ቤት እንድትገባ ትምህርቱን እንድትከታተል አደረጉ።

ሞዴል ፍቅር አፍሮ ፊንገርስና ኒው ሀብ የተሰኙ የሞዴሊንግና ፋሽን ትምህርት ቤቶች እንድትገባና ትምህርቷን እንድትከታተል አደረጉ፤ ትምህርቱን ለስድስት ወራት ተከታትላም ተመረቀች። በቆይታዋ ያገኘችው ብቃት ተረጋግጦ ዓለም አቀፍ ሞዴል መሆኗን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት አግኝታለች።

የኒው ሀብ የሞዴሊንግ ትምህርቷን ደግሞ በቅርብ የምታጠናቅቅ ሲሆን፤ ይህ ትምህርትም ለሞዴሊንግ ሙያ ብቁ የሚያደርጋት እውቀት ለማግኘት ያስችላታል። ይህ ጥረቷ ደግሞ ወደፊት ለመሆን ለምትፈልገው ዓለም አቀፍ ሞዴልነት የሚያበቃትን መደላድል የሚፈጥርላት ነው።

ሞዴል ፍቅር በመደበኛ ትምህርቷም ቢሆን በጣም ጎበዝ እና ታታሪ እንደሆነች ወላጆቿ ይናገራሉ። በትምህርቷም ይሁን በሞዴሊንግ ሙያዋ የሚገርም የራስ መተማመን እንዳላትም ይገልፃሉ። ሞዴል ፍቅር፤ በትምህርት ሰዓት ትምህርቷን ትከታተላለች፣ የሚያስፈልጋት ድጋፎች ሁሉ በወላጆቿ ይደረግላታል። ከትምህርት ውጭ ባሉ የእረፍት ጊዜዎቿ ደግሞ የሞዴሊንግ ሥራዎችን በመሥራት ጊዜዋን በአግባብ እንድትጠቀም ለማድረግ ጥረት እንደሚያደርጉም ወላጆቿ ይገልጻሉ።

በሞዴሊንግ ትምህርት ቤቶች በሚዘጋጁ ትርዒቶች ላይ ሥራዎቿን ማቅረቧን የምትናገረው ሞዴል ፍቅር፤ ብዙዎች የሰጧት አድናቆትና ማበረታታት ሙያውን ከአሁኑ አጥብቃ ይዛ ወደፊት ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሳ ሀገሯን ለማስጠራት እንድትችል የሚያደርጋት እንደሆነ ትናገራለች።

ሥራዎቿን አፍሮ ፊንገርስ ትምህርት ቤት ባዘጋጀው የፋሽን ሳምንት ላይ በመገኘት አቅርባለች። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የመጽሐፍት ምረቃ በሚካሄዱባቸው ቦታዎች፣ በቲክቶክ የፈጠራ ሥራ የሽልማት ሥርዓት እና ሌሎችም ዝግጅቶችና ሁነቶች ላይ ተጋባዥ በምትሆንበት ጊዜ ሥራዎቹን ማቅረቧን



**ሞዴል ፍቅር አሸናፊ**

አጫውታናለች።

ከዚህ በተጨማሪ በትምህርት ቤት በተከበሩ የአሸንዳና የኢሬቻ በዓላት ላይ የሀገሯን ባሕል የሚያስተዋውቁ አልባሳት በመልበስ የማስተዋወቅ ሥራ መሥራቷን ትናገራለች። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በቲክቶክ እና ኢንስታግራም (ሶሻል ሚዲያ ፕላትፎርም) ገጾች ላይ የምትሠራቸውን የሞዴሊንግ ሥራዎችና ፎቶዎችን በመልቀቅ የሀገሯን ባሕል ለማስተዋወቅ ጥረት እያደረገች ትገኛለች።

የሞዴሊንግ ሥራዎቿን የትምህርት ጊዜዋን በማይሻማ መልኩ እንደምትሠራ ወላጆቿም ይገልጻሉ። ለዚህም ወላጆቿ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ከጎኗ ሆነው እያገዟት እንደሆኑ ይናገራሉ።

የፍቅር ወላጆች የሞዴሊንግ እና የማስተዋወቂያ ሥራዎችን የሚያሠሩ ብዙ ኤጀንቶች ሥራዎችን ለማሠራት እንዳነጋገሯቸው ይናገራሉ። ሆኖም ግን እነዚህ ሥራዎች ከትምህርቷ ጋር እንዳይጋጩ በመፍራት ፍቃደኛ አልሆኑም። እነርሱ እንደሚሉት፤ በመደበኛ ትምህርቷ መታነጽ ስለሚኖርባት ትኩረቷ በዚያ ላይ መሆን አለበት። ራሷን ስትችል ግን በራሷ ተንቀሳቅሳ ዓለም አቀፍ ሞዴል የመሆን ሕልሟን እውን ለማድረግ ትችላለች ብለዋል ።

ሞዴል ፍቅር ሀገሯን የምትወድ ልጅ መሆኗን በሥራዎቿ እያሳየች ነው የሚሉት ወላጅ አባቷ አቶ አሸናፊ ተስፋዬ፤ ይቺ ትልቅ ራዕይ ያላት ታዳጊ የምታሰበው እንዲሳካላትና ዓለም አቀፍ ሞዴል ሆና ሀገሯን እንድታስጠራ ማገዝ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

በራስ መተማመን እንዲኖራት እና የምትፈልገውን መሆን እንድትችል የሚያበረታቷት ወላጆቿ እንደሆኑ የምትናገረው ሞዴል ፍቅር፤ ‹‹ በትምህርቴ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነኝ። መደበኛውን ትምህርቴንና የሞዴሊንግ ሙያን ጎን ለጎን እያስኬድኩት እገኛለሁ። ለወደፊት ዓለም አቀፍ ታዋቂ ሞዴል ሆኜ ሀገሬን ለማስተዋወቅ እፈልጋለሁ›› ብላለች። ልጆች በራስ መተማመን እንዲኖራቸው፣ ዝንባሌያቸውን አውቀው እና ስንፍናን አስወግደው ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ለማካሄድ ጥረት ማድረግ አለባቸው ስትል ትመክራለች።

ሞደል ፍቅር ‹‹በእድሜ ትንሿ ኢትዮጵያዊት ሞዴል›› የሚለውን ስያሜ ለማግኘት የሚያስችላት አስፈላጊዎቹን መስፈርቶች አሟልታ ሂደቶቹን በሙሉ ያለፈች ሲሆን፣ በቅርቡ የአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ ላይ ስሟ መስፈሩን የሚገልጽ ሰርተፊኬት እንደምታገኝ ወላጆቿ አስታውቀዋል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ስንፍናን እንደ ምቾት ማየት

**ዋሰልኝ አየለ**

አቶ መለስ ዜናዊ የፓርላማ አባላቱን ያሳቀ አንድ የተናገሩት ተረት ትዝ አለኝ። አንድ ድሃ ገበሬ ነበር፤ ገበሬው ድሃ ብቻ ሳይሆን ሰነፍ ነበር። ቤቱም ዝናብ ታፈሳለች። የሚያፈሰውን ጣሪያ ከመጠገን ይልቅ በማታፈሰው በኩል ይተኛል።

አንድ ሀብታም ገበሬ ደግሞ ዝናብ እየጣለ በዝናቡ ውስጥ ከብቶችን ያስገባል። አንዱን ሲያስገባው አንዱ ይወጣል። ሀብታሙ ገበሬ በዝናብ እየበሰበሰ ሲሯሯጥ ቤቱ ዝናብ የምታፈሰው ያ ድሃ ገበሬ በከፊል የምታፈሰው ቤቱ ውስጥ ሆኖ በቀዳዳ በኩል ሀብታሙን ገበሬ ያያል። የዚያን ታታሪ ገበሬ በዝናብ መመታት ሲመለከት ‹‹እንኳንም ድሃ ሆንኩ›› ብሎ ስንፍናውንና ድህነቱን በፀጋ ተቀበለ።

ይህን ያስታወሰኝ ሰሞኑን ያስተዋልኳቸው ሁለት ነገሮች ናቸው። ባለፈው ሐሙስ አንድ ጓደኛዬ ከቤት ግዥ ጋር በተያያዘ ምስክር ልሆነው ወደ አንድ የሰነዶች ማረጋገጫ ቢሮ ገባን። ብዙ አይነት ጉዳይ ስላለ ወከባውና ግርግሩ ብዙ ነው። በተለይ የቤት ጉዳይ ደግሞ ጣጣው ብዙ ነው። እዚያ ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፏል። እኔ ግን ለእነዚያ ሰዓታት እንኳን ሰለቸኝ። ስለአሰልቺነቱ ስናገር ‹‹ይሄማ በጣም ቀላሉ ነው እኮ! ዋናው ጣጣ አልቋል›› ብሎ ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶች ነገረኝ። እኔም እንደ ቀልድ ‹‹ከዚህ ሁሉ ግን ያለቤት ቢኖሩ ምን ችግር አለው?›› ስል ዙሪያዬን ያሉት ሁሉ ሳቁብኝ።

እንግዲህ አስቡት እሱ ብዙ ውጣ ውረድ አልፎ ቤት የመግዛት ደረጃ ላይ ሲደርስ፤ እኔ ለሰዓታት መታገስ ሰነፍኩ ማለት ነው። ምንም እንኳን በሰዓቱ እንደ ቀልድ ብናገረውም ያንን ሁሉ ትዕግስትና ትጋት ነበረኝ ወይ የሚለው ግን የምሬን ነበር ራሴን እንድጠይቅ ያደረገኝ።

ሌላኛው የታዘብኩት፤ ሰሞኑን በማኅበራዊ ገፆች አንድ የቢዝነስ ዕቅድ ዘመቻ ሲካሄድ ነበር። አንድ ባለሀብት ጥሩ የቢዝነስ ዕቅድ ላላቸው ሰዎች አወዳድሮ የ100 ሺህ ብር ሽልማት እንደሚሰጥ አሳወቀ። ውድድሩ የቢዝነስ ዝርዝር ሀሳባቸው ታይቶ ብዙ ‹‹ላይክ›› ያገኘውን መሸለም ነው። በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች ‹‹ላይክ›› አድርጉልን በማለት የጓደኞቻቸውን ስሞች በአስተያየት መስጫ ሳጥኑ ውስጥ ሲዘረዝሩ (በፌስቡክ ቋንቋ ሜንሽንድ ይባላል) ነበር።

ከዚያ ዘመቻ ውስጥ ያስተዋልኩት ነገር ብዙ ወጣቶች የፋይናንስ ድጋፍ ቢያገኙ የቢዝነስ ሀሳብ ያላቸው መሆኑን ነው። በዚሁ ጉዳይ ላይም ብዙ ሰዎች ሀሳባቸውን ሲሰጡ ነበር። ለካ ብዙ ሰዎች ብዙ ሀሳብ ማመንጨት የሚችሉ ናቸው። ለዚያውም እነዚያ ሀሳቦች ለረጅም ጊዜ ታስቦባቸው፣ ብዙ ጥናትና ምርምር ተደርጎባቸው የታሰቡ አይደሉም። ድንገት ዕድሉ ሲገኝ የውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የጻፏቸው ናቸው። በእርግጥ አንዳንዶቹ ምናልባት ዕድል በተገኘ ጊዜ በሚል ጽፈው ያስቀመጧቸው ሊሆኑም ይችላሉ። ወይም ጀምረዋቸው በአቅም ማጣት ምክንያት የተቋረጡ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ‹‹በአቅም ማጣት የተቋረጠብኝ ነው›› ብለው የገለጹም አሉ።

እዚህ ላይ ታዲያ በትልቁ የታዘብኩት ነገር ቢኖር ብዙ ስንፍናውን የተላመደ ሰው አለ። ስንፍናውን እንደ ምቾት በመቁጠር የሚያሾፍ ብዙ ሰው አለ። ለስንፍናው መሸፈኛ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ እንደ መሰናክል ያስቀምጣል። ጎበዝ የሆኑ ሰዎች አበርቱን ብለው ለጀመሩት ነገር ተስፋ አስቆራጭ የሆኑ አስተያየቶችን ይሰጣል። ‹‹በ100 ሺህ ብር ምንም የሚሠራ ሥራ የለም አርፋችሁ ተቀመጡ!›› አይነት ሀሳብ የሚሰጡ አሉ። ‹‹ዶሮ ሸጬ፣ ከሁለት ብር ተነስቼ...›› እያሉ መነሻቸውን የሚናገሩ ብዙ ባለሀብቶች ሰምተናል። ምንም እንኳን ያኔ የነበረው እና ዛሬ ብዙ ልዩነት እንዳለው ቢታወቅም፤ ቢያንስ ግን 100 ሺህ ብር ከድሮው 2 ብር ያንሳል? ንግድ ሲባል የግድ ከትልቅ ነገር መጀመር አለበት? ብዙዎቻችን የምንሸወደው በዚህ አመለካከት ውስጥ መሆናችን ነው።

እኔ ከዚያ ዘመቻ ውስጥ የተረዳሁት ነገር የብዙዎቻችን ችግር የገንዘብ ብቻ ሳይሆን የቢዝነስ ሀሳብ መሆኑን ነው። ራሴን የታዘብኩበት ነው። ለካ ገንዘቡ ቢገኝም ጥሩ የቢዝነስ ሀሳብ ከሌለ ዋጋ የለውም! ብዙዎች የሚከስሩትም በዚህ ምክንያት መሆን አለበት። ይህን ያህል ብር ባገኝ ምንድነው የማደርግበት? የሚለውን ማሰብ ብልህነት ነው። የብዙዎቻችን ችግር ግን ከገንዘቡ በላይ ሀሳቡ ነው። ዛሬ ዓለምን እያሽከረከሩ ያሉ ትልልቅ ካምፓኒዎችና የቴክኖሎጂ ውጤቶች መጀመሪያ በሀሳብ የተጀመሩ ናቸው።

የድህነት አደገኛው ምክንያት ስንፍናን እንደ ምቾት ማየት ነው። ልክ እንደ ሰነፉ ገበሬ ዝናብ ከሚመታኝ ቢርበኝ ይሻለኛል እንደማለት ነው። ለራሱም፣ ለቤተሰብም፣ ለሀገርም ሸክም ይሆናል ማለት ነው። ልክ እንደ ግዑዝ አካል እሱ ሳይንቀሳቀስ መኖርና መብላት ነው የሚፈልግ፤ ይሄ ደግሞ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ውጭ ሆነ ማለት ነው። ስንፍና በሃይማኖትም፣ በሳይንስም፣ በማኅበራዊ ሕይወትም የተወገዘ ነው። ብዙዎቻችን ግን ይህን ሁሉ ጥሰን ሰነፎች ነን። የአንዳንዶች ደግሞ ይባስ ብሎ ሰነፍ መሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ሰነፍ ለማድረግ ተግተው የሚሠሩ መሆናቸው ነው።

በእርግጥ አንድን ነገር ለመከወን በሀገራችን አሠራር ውስጥ ብዙ አሰልቺ ውጣ ውረድ አለ። ችግሩ ግን ያ አሰልቺ ውጣ ውረድ የመጣው ከስንፍናችን መሆኑ ነው። ሁላችንም ንቁ፣ ታታሪና ኃላፊነት የሚሰማን ቢሆን ልክ እንደ ሠለጠኑ ሀገራት ቀልጣፋ አሠራር ይኖረን ነበር። ነገሮችን በፍጥነት ለመሥራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት (ሲስተም) ይኖረን ነበር። ሰነፎች ስለሆንን ግን ያንን መዘርጋት አልቻልንም፤ በዚህ አያያዝ ለልጆቻችን የምናወርሳቸው እንደዚሁ ውስብስብ አሠራር ያለበት አገርና ሥርዓት ይሆናል ማለት ነው።

ስንፍናን እንደ ምቾት መላመድ ምቾት ሊመስል ቢችልም ውስጡ ግን በሽታ አለበት። አንድ ሰው ታታሪ ሆኖ ሲለፋ ቢውል ምናልባት አካሉ ቢደክም ነው፤ የስንፍና ችግሩ ግን አካልን ሳይሆን አዕምሮን ነው የሚያደክም፤ ድብርት የሚባለው መጥፎ ነገር የሚመጣው ምንም ካለመሥራት ነው። እርግጥ ነው ከፍተኛ የሥራ ጫና ውጥረት እንደሚፈጥር ይታወቃል፤ ዝም ብሎ እንደመቀመጥ ግን አደገኛ ነገር አይኖርም።

አንድ ቀላል ምሳሌ ላንሳ። ለምሳሌ ይህ ገጽ የኔ ነው። ይህ ጽሑፍ ለሰኞ ታኅሣሥ 8 ቀን እንደሚወጣ ረቡዕ ወይም ሐሙስ ተነገረኝ እንበል። እሁድ እሠራዋለሁ ብዬ ብቀመጥ ዓርብ እና ቅዳሜ ነፃ መሆን አልችልም። አለብኝ የሚለውን እያሰብኩ ነው የምቆየው። ወዲያውኑ ጨርሼ ባስረክብ ግን ነፃ ሆንኩ ማለት ነው። ስለዚህ ሥራ ሳይሆን ስንፍና ነው ማለት ነው ለጭንቀት የሚዳርግ።

ቢቻል ሁላችንም ታታሪ ብንሆን፤ ያ ባይሆን እንኳን ቢያንስ ግን ሌሎችን ባናሳንፍ!

## ነፃ ሃሳብ

# በሀገር ላይ ሌብነት ሁሉን አቀፍ ክስረት ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አንዳንድ ኩነቶች እንደብርቱ መነሻቸው ብርቱ መውደቂያም አላቸው። ሀገር በታሪክ፣ በሥራ፣ በትጋት፣ በአብሮነት እንደምትጸና ሁሉ የሚጥላትም እንደሙስና ያሉ ራስ ተኮር አስተሳሰቦች ናቸው። አብዛኞቹ ሀገራት በብልሹ አሠራር በተከፈተ የሙሰኞች አመል ወድቀዋል ለመውደቅም እየተንገዳገዱ ናቸው።

በዚህ ዓውድ ውስጥ መውደቅ ማለት ከታሪክ መጥፋት አሊያም ደግሞ አለመኖር አይደለም። መውደቅ ማለት በእድገትና በብልጽግና ወደ ኋላ መቅረት ማለት ነው። ብዙኃኑን የረሳ፣ መሐሉን የዘነጋ ተጠያቂነት የሌለው ሕገ ወጥ ቅብብሎሽ ማለት ነው። ሕግና መርሕን ባልተከተለ ራስወዳድነት የሀገርን ሀብት ለግል ጥቅም በማዋል ብዙኃኑ ላይ መከራን ማወጅ ማለት ነው።

በሀገር ላይ ሌብነት ሁሉን አቀፍ ክስረት መሆኑን ለማመን በሙስናና በብልሹ አሠራር የደረሰብንንና እየደረሰብን ያለውን ስርቆትና ውድመት ማሰቡ በቂ ነው። የሰው ልጅ በእንቅፋት ተመቶ ይወድቃል አሊያም ይደነቃቀፋል። የሀገር መደነቃቀፍ በሙሰኞች አመል ውስጥ ያለ ነው። መደነቃቀፍ ጸንተን እንዳንቆምና ወደፊት እንዳንሄድ የሚያደርግ ነው።

ሙስና መነሻው የተለያየ ቢሆንም የስብዕና ግድፈት የሚለው ግን ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል። በስብዕናቸው የተመሰገኑ ሰዎች የሌላን ለመንካት የሞራል ልዕልና የላቸውም። ሀገር በማገልገል ጊዜና ጉልበታቸውን የሚሰዉ ናቸው። በተቃራኒው በስብዕናቸው ጤነኛ ያልሆኑ ግለሰቦች በስርቆትና በሌብነት በሌላም መልካም ባልሆነ ተግባር በሀገር ላይ መከራ ለማዝነብ የሚቀድማቸው የለም።

በብልሹ አሠራር እየተመዘበረ ያለው የሕዝብ ሀብትም በነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች መሪነት የሆነ ነው። ንቅናቄአችን መጀመር ያለበት ስለሀገር ሲሉ ታማኝ የሆኑትን በማመስገን እና ነውረኞችን በመቅጣትና በማጋለጥ ነው። ታማኝ አገልጋዮች ካልተመሰገኑ በሕዝብ ስም የሚነግዱ አስመሳዮች ከጥፋታቸው አይታረሙም።

ሙስና በብልሹ አሠራር ተጀምሮ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ሲሆን በተጨማሪ ከየትኛውም አደገኛ ሁኔታ በላይ ጎጂ መሆኑን ለመገንዘብ ጠቢብ መሆን አይጠይቅም። ሥልጣንና ኃላፊነታቸውን ወደጎን ብለው በማን አለብኝነት ከድሀ ሕዝብ ላይ የሚሰርቁ ብዙ ባለሥልጣናት አሉ።

ማይክ በጨበጡ ቁጥር ሙስና ጎጂ ነው፣ አዋራጅ ነው የሚሉ በተግባራቸው ግን የቀለሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት ለሕዝብ በተከፈተ በራፋቸው ብዙ መሰል ነውረኞችን አመላልሰዋል። ከፌዴራል እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ለምንም ነገር እጅ መንሻ የሚጠይቁ ተበራክተዋል። አንዳንዶቹ ከተጠያቂነት ወደእውቅና ወርደው ነውርነታቸው ቀርቶ ገሀድ ወጥተው በግልጽ ወደመሆን የመጡ ናቸው።

ሙስና በጭቃ ሲለወስ መልኩ እንደሚጠፋ አንድ ፀዓዳ ቁስ ልናስበው እንችላለን። የፀዓዳውን ቁስ ውበት ጭቃው ሸፍኖታል። ጭቃው እስካልጠራ ድረስ የቁሱ ውበት አይታይም። ሀገርም እንዲህ ናት..ሙሰኞች እስካልጠፉ ድረስ እድገቷ ብልጽግናዋ አይታይም። ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እስካልሰፈነ ድረስ ሕልምና ራዕዮቻችን አይሰምሩም። ጥቂቶች ጠግበው ብዙኃኑ በተራበባት ሀገር ላይ፣ ጥቂቶች ደልቷቸው የተቀረው በተከፋበት ሁኔታ ሁሉን አቀፍ ውድቀት ካልሆነ በስተቀር ሁሉን አቀፍ ለውጥ አይመጣም።

ሁሉን አቀፍ ለውጥ የሚመጣው ሁሉን አቀፍ በሆነ ሚዛናዊ አስተሳሰብና ትግባሬ ነው። ሁሉን አቀፍ ውድቀት ለመፍጠር ቀላል ነው ሙስና ብቻውን በቂ ነው። የሙስናን አደገኛነት ለመግለጽ ብዙ የቅርብና የሩቅ ታሪኮችን ማስታወስ ይቻላል። ብዙ መብራትና ውሀ፣ ሆስፒታልና ትምህርት ቤት የሚገነባ ገንዘብ ወደአንድ ሰው ኪስ ሲገባ፣ ብዙ ድሃዎችን የሚታደግ የሕዝብ ንብረት ወደሆኑ ቡድኖች ካዝና ሲገባ፣ የተለያዩ የሕዝብ መገልገያ መሠረተ ልማቶችን የሚሠራ ረብጣ በሆኑ ሰዎች እጅ ሲገባ አይተናል፤ ለዚህ እንግዶች አይደለንም።

እንደመንግሥት እና እንደዜጋ ትልቁ ትግላችን ሊሆን የሚገባው የሙሰኞችን ሰንሰለት መበጠስ ላይ ነው። በእኩል ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ አስተዳደራዊም ሆነ ተገልጋይነትን ለማስፈን ትልቁ መነሻችን ሊሆን የሚችለው ግልጽነት የሰፈነበት የተጠያቂነት አሠራር ነው። ሙሰኞችን ማጋለጥና ለሕግ የማቅረብ አሠራር ድህና ኋላ ቀር በሆነች ሀገር ላይ እንዲሁም ራሱን በምግብ ለመቻል ደፋ ቀና በሚል ሕዝብ ውስጥ ዐበይት ጉዳይ ነው።

ተግዳሮቶቻችንን ወደ በረከት ለመቀየር ሀገር የቀደመችበት የአመራር ጥበብ ያስፈልገናል። ራሳችንን አስቀድመን ትውልዱን በማስከተል የምንመራው ፖለቲካ፣ የምንወደው ሕዝብ፣ የምናልመው ሕልም ትርጉም አልባ ነው። ከእንዲህ አይነቱ መሠረታዊ ችግር ስንወጣ ነው ለአዲስ ለውጥ በር የምንከፍተው።

በሥርዓት ካላደግን ሕዝብ በማገልገል ረገድ በበጎ የሚጠቀስ ስም አይኖረንም። በግብረገብነት አድገን ከሆነም በእኩይ ምግባር ሀገር ለማዋረድ እድል ፈንታ አናገኝም። ለኢትዮጵያ መከራ የሆኑባት ከአስተዳደግ ጀምሮ ባለው ታሪካቸው ላይ አግድም ያደጉ ከእምነትና ከሥርዓት ያፈነገጡ ናቸው። ድምፅ ማጉያ ሲይዙ አፋቸው የሚያወራ በተግባር ሲፈቱ ግን እዚህ ግባ የማይባሉ ዱባና ቅሎች።

ሙስና ዓለም አቀፍ ችግር ቢሆንም ጎልቶ የሚገኘው እንደእኛ ባሉ በአስተሳሰብና በሥልጣኔ ባልዳበሩ ሀገራት ውስጥ ነው። ሥልጡኖቹ ሀገራት ሀገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስለገባቸው ከራሳቸው ላይ ለሀገር ይሰጣሉ እንጂ ማንም አላየኝም ወይም አያየኝም ብለው ከሀገራቸው ላይ ለራሳቸው አይሰርቁም።

ይሄ የሀገር ፍቅር ጽንሰ ሀሳብ ነው በሥልጣኔም በዘመናዊነትም ላይና ታች ያስቀመጠን። ሀገር ማለት ምን እንደሆነ ሲገባን እንደሥልጡኖቹ ከሕዝብ ላይ አንሰርቅም። ካልገባን ግን በመስረቅና በማሰረቅ ከበር ከፋቾቹ እንደአንዱ በመሆን ሀገር እናራቁታለን።

ሙስናና ሙሰኞች ሀገር በመለወጥ ትግል ውስጥ ሁሉም የድርሻውን እየተወጣ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ተጋድሎን የሚያደናቅፉ፣ ተስፋን የሚያደበዝዙ የብርሀን ጽልመቶች ናቸው። እኚህ ጽልመቶች ሲገፈፉ ብቻ ነው እንደ ሀገር ብርሀን የሚወጣልን። በሥልጣንና በአለቅነት ብርሃናችንን ጋርደው ቆመዋል። በተጠያቂነት መርሕ ገለል እንዲሉ ስናስገድዳቸው ያኔ ሁሉም ነገር አዲስ ይሆናል።

ዓለም ስለሙስና መክራና ዘክራ ታውቃለች። እየቀጣችና እያስጠነቀቀች፣ እየሸለመችና እያወደሰች ዓመታትን ዘልቃለች። ሰሞኑን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ20ኛ ጊዜ ‹ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው በኅብረት እንታገለው› በሚል መሪ ሀሳብ የፀረ ሙስና ቀን ተከብሯል።

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በኩልም ፕሮግራሙን በሚዘክሩ የተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሮ ውሏል። በመዝጊያ ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አበቤ ‹ሙስናና ሙሰኞች ላይ የሚደረገው ትግል የታይታ መሆን የለበትም እንደሀገር ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጣ መሆን አለበት› ሲሉ አጽንኦት የሰጡበትን ንግግር ማስታወስ ያስፈልጋል።

ከዚህ ጋር አያይዘውም ‹ሙስና የሀገርን እድገት በእጅጉ እንደሚጎዳና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር በማድረግ በእውነት ላይ ያልቆመ የድህነትና የሀብት ልዩነትን የሚፈጥር በተጨማሪም ሀገር ገቢዋን እንዳትሰበስብ እክል የሚፈጥር ነው› ሲሉ ጥቁምታ አስቀምጠዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ሀገራዊ ስጋቱን በመመልከት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ ደረጃ የፀረ ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም የፀረ ሙስና ትግሉን ከሆነ ስፍራ አውጥቶ ተቋማዊና ሀገራዊ ለማድረግ ይሁንታ የሚያሳይ ሥራ እየሠራ እንደሆነ በክቡር ከንቲባዋ በኩል መገለጹ ትግሉን የሚያበረታና ይበል የሚያሰኝ እንደሆነ ያመላክታል። በመስተዳድር ደረጃ እንዲህ ያለ የትግል ንቅናቄ ለዛውም ተቋማዊ በሆነ አሠራር መጀመሩ መጪውን ጊዜ በበጎ እንድንቃኝ የሚያደርግ ነው።

ከዚህ ቀደም ስለሙስና የተለያዩ ሀሳቦችን የተለዋወጥንባቸው የተለያዩ መድረኮችን አስተናግደናል። ሀሳቦቻችን ለውጥን ሲያመጡልን ግን አልታዩም። ይሄ ማለት ከንግግር ባለፈ ወደተግባር የሚወስድ ብርታትና ቁርጠኝነት አላዳበርንም ማለት ነው። ከዚህ ረገድ የተነጋገርንባቸውን ሀሳቦች መለስ ብሎ በማጤን ለትግበራ ቁርጠኛ መሆን ሙሰኞችን ለመዋጋት ቀዳሚው ነገር ነው።

ሙስናን ከመከላከል ረገድ እንደዋና መፍትሔ ከተጠቀሱ ሀሳቦች ውስጥ ቀዳሚዎቹ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ናቸው። አሁን ባለው የአገልጋይና የተገልጋይ መስተጋብር ውስጥ የተባለውን ያክል ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንደሌለ ብዙዎች ይስማሙበታል። ይሄ አይነቱ አካሄድ ብልሹ አሠራርን በማበረታታት ሥልጣንን ያለአግባብ ወደመጠቀም መርቶናል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው የመፍትሔ አካል አሠራርን ማዘመን የሚለው ነው። አሠራርን ማዘመን ማለት ከአስተሳሰብ ጀምሮ፣ ተገልጋይ ተኮር የሆነ እንቅስቃሴን እንደመርሕ በመውሰድ በቴክኖሎጂና በሀገር ፍቅር በታገዘ ሃላዊነት መመራት ማለት ነው።

ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ከዘመነ አሠራር እና በሥርዓት ከተቃኘ ኃላፊነት ጋር ተዋሕደው ሲቀርቡ ነው ሙሰኞችን በማጋለጥ ሀገር የምንታደገው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ትውልዱን እንደአዲስ የሚቀርጹ የሥርዓትና የግብረገብነት አካላት መኖራቸው የሚያጠያይቅ ባይሆንም የመጣንበት ‹ያበላል እንዴ? እና ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል› አይነት እኩይ አመለካከቶች የዛሬዋን በሁሉ ነገሯ ስንኩል የሆነችን ሀገር እንድንፈጥር አስተዋፅዖ አዋጥተዋል ብዬ አስባለሁ።

ከእንዲህ አይነቱ ማንንም በኩራት ካላራመደ አስተሳሰብ ወጥተን ሀገር ተኮር እና ማኅበረሰብ መር በሆነ የሥርዓት አቅጣጫ ብንመራ የተሻለ ነው ባይ ነኝ። በዚህ ረገድ የሃይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት አለባቸሁ።

በሞራል የተገነባ፣ በተጠያቂነት የጎለመሰ ትውልድ በሥራው ምስጋና ይቸረዋል እንጂ ማንም ጣት አይጠቋቆምበትም። ሙስንና የሚያጋልጥ እና ለምን ብሎ የሚጠይቅ ትውልድ በሌለባት ሀገር ላይ ለውጥ የማይታሰብ ነው። የሆነ አካል ሲሰርቅና ሲያሰርቅ ስናይ መጠቆም ኃላፊነትን ከመወጣት ጎን ለጎን ሙስናን ለማድረቅ እየሄድንበት ያለውን ንቅናቄ የሚያሳልጥም ነው።

ሙስና በአንድ ሀገር ላይ እንደ እከክ ነው። እከክ በወቅቱ ካልታከመ ሰውነትን የሚወርስ ከዛም ወደቁምጥና የሚወስድ ደዌ ነው። ሙስናንም ከዚህ ለይተን ልናየው አንችልም። አነሳሱ ቀላል ቢመስልም መሐሉና ዳሩ ሀገርን አቆርቁዞ፣ ትውልድን አደህይቶ ከድጥ ወደማጥ የሚያስገባ እኩይ ተግባር ነው።

እንደሀገር ብዙ ማኅበራዊ ተግዳሮቶች ቢኖሩብንም የሙስናን ያክል እየጎዳንና እያራቆተን ያለ ችግር ግን የለም። ሙስና ብዙኃን የሚጠቀሙበት ሳይሆን ጥቂቶች ኪሳቸውንና ሆዳቸውን የሚያደልቡበት ነው። ችግሩን ሕዝባዊ ያደረገው ደግሞ ወደአንድ ግለሰብ ኪስ ወይም ካዝና የሚገባው ሀብት የሀገር ንብረት የሕዝብ ላብ እና ድካም መሆኑ ነው። በዚህ ረገድ ሙስናን ለመከላከል ቁርጠኞች እንሁን።

> **እንደመንግሥት እና እንደዜጋ ትልቁ ትግላችን ሊሆን የሚገባው የሙሰኞችን ሰንሰለት መበጠስ ላይ ነው። በእኩል ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ አስተዳደራዊም ሆነ ተገልጋይነትን ለማስፈን ትልቁ መነሻችን ሊሆን የሚችለው ግልጽነት የሰፈነበት የተጠያቂነት አሠራር ነው**

# ዓለም አቀፍ

## ትራምፕ ስደተኞች "ደማችንን እየበከሉ ነው" የሚለውን ንግግራቸውን ደገሙት

በጋዜጣው ሪፖርተር

ትራምፕ ስደተኞች "ደማችንን እየበከሉ ነው" የሚለውን ንግግራቸውን ደግመውታል።

ሪፐብሊካንን በመወከል ለፕሬዚዳንትነት የሚወዳደሩት ዶናልድ ትራምፕ ስደተኞች "የሀገራችንን ደም እየበከሉ ነው" በማለት ከዚህ በፊት በዘረኝነት እና የናዚን መፈክር በማስተጋባት ትችት ያስነሳባቸውን ንግግር ደግመውታል።

ትራምፕ ይህ ያሉት ከሜክሲኮ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስደተኞች በሚገቡበት ኒው ሄሚስፌር ግዛት ባደረጉት የምርጫ ቅስቀሳ ላይ ነው።

ትራምፕ ለአራት ዓመት የሥልጣን ዘመን በድጋሚ የሚመረጡ ከሆነ በሕገወጥ ስደትን እንደሚያስቆሙ እና በሕጋዊ ስደተኞች ላይ ደግሞ ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

ትራምፕ ለደጋፊዎቻቸው ስደተኞች ከደቡብ አሜሪካ በተጨማሪ ከአፍሪካ፣ ከእስያ እየመጡ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ትራምፕ ናሽናል ፐልስ ከተባለው የቀኝ ዘመም ዌብሳይት ጋር ባለፈው መስከረም ወር መጨረሻ ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስደተኞች "ደማችንን እየበከሉት ነው" የሚል ተመሳሳይ ንግግር አሰምተው ነበር።

በወቅቱ ይህ የትራምፕ ንግግር "ዘረኝነት እና ጥላቻ" የሚያንጸባርቅ ነው የሚል ትችት አስነስቶ ነበር።

የያሌ ፕሮፌሰር እና በዘረኝነት ጉዳይ መጸሀፍ ያሳተሙት ጀናታን ስታንሊ ትራምፕ ቋንቋውን ደግመው መጠቀማቸው አደገኛ ነው ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ እንደተናገሩት ትራምፕ የጀርመኖች ደም በደዊሾች እየተበከለ ነው የሚለውን የሂትለር ንግግር ያስተጋባ ነው ሲሉ ተችተውታል።




ስታሊ"ትራሞፕ ይህ ቃል በሁሉም የድጋፍ ሰልፎች ላይ እየደገሙት ነው። አደገኛ የሆኑ ንግግሮችን መደጋገም እንዲለመዱ ያደረጋል" ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ እንደተናገሩት ይህ በአሜሪካ በሚኖሩ ስደተኞችን ስጋት ላይ እንዲወድቁ ያደርጋል።

ባለፈው ጥቅምት ወር የትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቃል አቀባይ ስቴቨን ቹንግ እንዲህ አይነት ቃላት በመጽሀፍ፣ በዜና እና በቴሌቪዥን የተለመድ ናቸው በማለት በትራምፕ የቀረበውን ትችት "ትርጉም የለሽ" ሲሉ አጣጥለውት ነበር ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

## የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ጃኮብ ዙማ አዲስ ፓርቲ መሠረቱ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ጃኮብ ዙማ አዲስ ፓርቲ ማቋቋማቸውን ገለጹ።

ለ19 ዓመታት ደቡብ አፍሪካን በፕሬዚዳንትነት የመሩት ዙማ፥ በቀጣዩ ጠቅላላ ምርጫ ለመሠረቱት አፍሪካ ናሽናል ኮንግረንስ (ኤኤንሲ) እንደማይቀሰቅሱና ድምጽ እንደማይሰጡም ነው የተናገሩት።

"ኡምክሆንቶ ዊ ሲንዜ" ወይም በምህጻሩ "ኤምኬ" የሚል ስያሜ ያለው አዲስ ፓርቲያቸው የቀድሞውን የኤኤንሲ ወታደራዊ ክንፍ ስያሜ ወስዷል። ዙማ አባል የነበሩበትና የአፓርታይድ አገዛዝን የተዋጋው ወታደራዊ ሃይል "ኤምኬ" በ1994 ኔልሰን ማንዴላ ወደ ሥልጣን ከመምጣታቸው አንድ ዓመት ቀደም ብሎ መፍረሱ ይታወሳል።

ጃኮፕ ዙማ በሶዌቶ በሰጡት መግለጫ፥ የቀድሞው "ኤምኬ" በነፍጥ የአሁኑ "ኤምኬ" ደግሞ በምርጫ ይፋለማል ሲሉ ተናግረዋል። "ራሳችን አሳልፈን የሰጠንለት ኤኤንሲ አሁን ተጠልፏል" የሚሉት ዙማ፥ በ2018 የተኳቸው ሲሪል ራማፎሳን ፓርቲውን ወደ ቁልቁለት እየገፉት ነው በማለት ወቅሰዋል።

"የራማፎሳ ኤኤንሲ በጥቁር ባለሙያዎች እና ምሁራን ላይ ጦርነት አውጇል፤ የታገልናቸው የነጭ የበላይነት አቀንቃኞች ወዳጅ ሆኗል" በሚልም ፓርቲውን ለመታደግ ትግል ጀምሬያለው ነው ያሉት።

በቀጣዩ ምርጫ ለኤኤንሲ ድምጽ መስጠትም የአፓርታይድ አገዛዝን እንደመደገፍና ሕዝብን እንደመካድ ይቆጠራል ሲሉ ተደምጠዋል። ዙማ አዲስ ፓርቲ ቢያቋቁሙም የኤኤንሲ አባል ሆነው እንደሚቀጥሉ መናገራቸውን ሬውተርስ ዘግቧል።

ደቡብ አፍሪካ ባደረገችው የጸረ አፓርታይድ አገዛዝ ትግል ውስጥ የተሳተፉትና ለዓመታት በእስር ያሳለፉት አወዛጋቢው



ሰው ጃኮብ ዙማ፥ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በ2018 ከሥልጣናቸው መልቀቃቸው ይታወሳል።

በ2021ም በተከሰሱበት ወንጀል ፍርድ ቤት አልቀርብም በማለታቸው ለእስር መዳረጋቸው አይዘነጋም።

የዙማ እስር ከፍተኛ ተቃውሞና አመጽ አስነስቶ ከ350 በላይ ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉና ከህክምና ጋር በተያያዘ ከሁለት ወራት ቆይታ በኋላ ከእስር መለቀቃቸው የሚታወስ ነው።

በዙማ የፕሬዚዳንትነት ዘመን ምክትላቸው የነበሩት ሲሪል ራማፎሳ ሙስናን ለመከላከል የያዙት አቋም በቀድሞው ፕሬዚዳንት የተወደደ አይመስልም።

ከሥልጣን ቢነሱም በርካታ ተከታይ እንዳላቸው የሚነገርላቸው ጃኮብ ዙማ "ኤኤንሲን ከአፓርታይድ አቀንቃኞች ለመታደግ" በሚል አዲስ ፓርቲ አቋቁመው ራማፎሳ ላይ ተነስተውባቸዋል።

ከግንቦት እስከ ነሃሴ 2024 ባለው ጊዜ ውስጥ በሚደረገው ምርጫ በሙስና እና ብልሹ አሠራር ወቀሳው የበዛበት ኤኤንሲ ከሌሎች ፓርቲዎች ብርቱ ፉክክር ይጠብቀዋል ተብሏል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# አበበ ቢቂላ በጃፓኗ ከተማ የታሰበበት የግማሽ ማራቶን ውድድር

ቦጋለ አበበ

ፈር ቀዳጁ ጀግና ኢትዮጵያዊ አትሌት አበበ ቢቂላ ከአምስት አስርተ ዓመታት በፊት የሠራው ዘመን አይሽሬ ታሪክ ዛሬም ህያው ነው። እኤአ በ1960 የሮም ኦሊምፒክ ማራቶን የባዶ እግር ገድል የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ሕዝቦች ድል ሆኖ ዛሬም ድረስ ይዘከራል። አበበ በሮም የጀመረው ወርቃማ ታሪክ ከአራት ዓመት በኋላም በቶኪዮ 1964 ኦሊምፒክ ማራቶን ቀጥሏል። ይህም የታላቁን አትሌት ድሎች ከጥቁር ሕዝቦች ባለፈ መላው ዓለም ሁሌም በልዩነት እንዲያስቡትና እንዲያከብሩት አድርጓቸዋል።

ሻምበል አበበ ቢቂላ በተለይም ሁለተኛ የኦሊምፒክ የማራቶን ድሉን በዓለም ክብረወሰን ታጅቦ ባስመዘገበባት የሩቅ ምስራቋ ሀገር የተለየ ክብር ይሰጠዋል። ጃፓን ለአበበ ካላት ትልቅ ክብር የተነሳ ኢትዮጵያዊውን ጀግና በብዙ መልኩ በመዘከር የሚስተካከላት የለም። ጎዳናዎችንና ድልድዮችን በተለያዩ ከተሞቿ በስሙ ሰይማለታለች። በቅርቡም እሱን የሚዘክር ትልቅ ሙዚየም አቋቁማለታለች። ከዚያ በላቀም አበበን እንደ አንድ የፅናት ተምሳሌት አድርጋ በሥርዓተ ትምህርቷ ውስጥ ያካተተች ሀገር ናት።

ጃፓን ኢባራኪ ግዛት በምትገኘዋ ካሳማ ከተማ የምታካሂደውን ዓመታዊ የግማሽ ማራቶን ውድድር ከ2012 ጀምሮ በጀግናው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ስም ሰይማለች። ይህ ውድድር ትናንት ሲካሄድም ከ 1600 በላይ ሯጮች ተሳትፈዋል።

በጃፓን የኢፌዴሪ አምባሳደር ዳባ ደበሌ የግማሽ ማራቶን ውድድሩን ያስጀመሩ ሲሆን፣ መሰል ወድድሮች ረጅም ዘመናት ያስቆጠረውን የሁለቱን ሀገራት መልካም ግንኙነት እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ይበልጥ አጠናክሮና አስተሳስሮ ለማስቀጠል ሚናው የጎላ መሆኑን ገልፀዋል። የጃፓን መንግሥት ይህን ውድድር በማዘጋጀቱና የጀግናው አትሌት አበበ ቢቂላ መታሰቢያ በማድረጉም ምስጋና አቅርበዋል።

የካሳማ ከተማ ከንቲባ ሺንጁ ያማጉቺ በበኩላቸው፣ የከተማው አስተዳደር ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር እየሰራ ያለውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡ በቀጣይ ከከተማዋ አስተዳደር የተውጣጣ ልዑክ በመምራት ኢትዮጵያን እንደሚጎበኙና ከኢትዮጵያ ከተሞች ጋር ግንኙነት በመመስረት በትብብር መሥራት እንደሚፈልጉ መግለጻቸውን በጃፓን የኢትዮጵያ ኤምባሲ መረጃ አመልክቷል።

650 አትሌቶችን በማሳተፍ የተጀመረው ይህ ውድድር ከዓመት ወደ ዓመት የተሳታፊዎቹን ቁጥር እያሳደገና እውቅናውም እየጨመረ ይገኛል። በጃፓን በሚካሄዱ የተለያዩ የማራቶን ውድድርሮች ማሸነፍ የቻሉ እንደ አበበ መኮንን አይነት አትሌቶችም ባለፉት ዓመታት በውድድሩ ላይ በተጋባዥነት ተገኝተው ሲያስጀምሩ እንደነበር ይታወሳል።

ውድድሩ በሚካሄድበት ወቅት የጃፓኗ ከተማ ካሳማ ነዋሪዎችና ባለሥልጣናት እንዲሁም በጃፓን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚታደሙ ሲሆን የኢትዮጵያ ባህላዊ የቡና



በአበበ ቢቂላ መታሰቢያ ውድድር ከ1600 በላይ ሯጮች ተሳትፈዋል፣

ማፍላት ሥነሥርዓትም የውድድሩ አንድ ድምቀት ሆኖ ቀጥሏል።

በተመሳሳይ አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮጦ ያሸነፈበትን የማራቶን ውድድር በማስመልከት በጣሊያኗ ሮም ከተማም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የመታሰቢያ ሩጫ ውድድሮች እየተካሄዱለት ይገኛሉ። አበበ ቢቂላ በ1952 ዓ.ም በጣሊያን መዲና ሮም በተካሄደ 17 ኛው የኦሊምፒክ ማራቶን ውድድር በባዶ እግሩ በመሮጥ 2 ሰዓት ከ 15 ደቂቃ ከ 16 ሴኮንድ በመግባት ታሪካዊ ድል ማስመዝገቡ ይታወሳል።

የአበበን ዘመን ተሻጋሪ ድል አስመልክቶ የመታሰቢያ የሩጫ ውድድር ከ60 ዓመት በፊት አትሌት አበበ ቢቂላ በሮጠበት ተመሳሳይ ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት በሮም "ተርሜ ዲ ካራካላ" ስቴዲየም የድሉ መታሰቢያ የሩጫ ውድድር በሮም በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲና ነዋሪነታቸውን እዚያ ባደረጉ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም "ACSI Italia Atletica" የአትሌቲክስ ክለብ ትብብር ይካሄዳል።

ይህ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ ከሶስት ዓመት በፊት መካሄድ ሲጀምር በውድድሩ 106 ሯጮች የተሳተፉ ሲሆን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በአንድ ላይ ሯጮችን ማስጀመር ባለመቻሉ የመጀመሪያው ሯጭ 195 ሜትር እንዲሁም ሌሎች ቀሪ 105 ሯጮች እያንዳንዳቸው 400 ሜትር እንዲሸፍኑ ተደርጎ ነበር። የሮም ከተማ ማህበረሰብና የተለያዩ የስፖርት ዘርፎች ኃላፊዎች በስታዲየም ተገኝተውም ውድድሩን ይከታተላሉ።

ከውድድሩ በተጨማሪ የቡና አፈላል ሥነ ሥርዓት እየቀረበ የአትሌት አበበ ቢቂላ፣ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብት እና መዳረሻዎች፣ የኢትዮጵያ ምድረ ቀደምትነትና የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ለታዳሚዎች በመቅረብ ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ ሥራዎች ይሠራሉ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ